የኤርትራ ፕሬዝዳንት አማካሪ፣ ማስታወቂያ ሚ/ሩና የደህንነት ሹሙ በሕገ ወጥ የመሳሪያ ዝውውር ተወነጀሉ 13




የንጉ/ሥ ልደት ሲከበር
ቴዲ ለመጀመርያ ጊዜ አቀነቀነ 14



አሸናፊው ማነው?
በፕሮፌሰር መሳይ ከበደ 3

ምርጫ 2002 እና የጠ/ሚ መለስ አዲሱ ስትራቴጂ 5




# አውራምባ ታይምስ
ለመረጃ ቅርብ ይሁኑ

2ኛ ዓመት ቁጥር 83 መስከረም 19 ቀን 2002 ዋጋ 3.50 ብር




Photo: Sisay Guzay for Awramba

13

ቴዲ አፍሮ ከሳምንት በኋላ፡-

# የመጀመሪያውን ታላቅ ኮንሰርት በስታዲየም

## ከሲያትልና ቺካጎ በሚመጡ ሙዚቀኞች ዝግጅቱ ይደምቃል

## ገቢው ለችግረኞች መርጃ ይውላል

# ኤዲቶሪያል

# ከፖለቲካ ወገንተኝነት የጸዱ፣ነጻና ኃላፊነት የሚሰማቸው ሲቪክ

# ማህበራት ያስፈልጉናል!

«ዴሞክራሲ ብቻውን ሲቪል ማህበራት የሚጠናከሩበትን እድል አይፈጥርም። የዴሞክራሲ ስኬት የተመካው ግን በሲቪል ማህበራት ጠንካራ ተሳትፎ ነው» የሚል ወርቃማ አባባል አለ። የሲቪክ ድርጅቶች በማሕበረሰቡ ውስጥ ባላቸው ገንቢ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱትን የችግር ፈቺነት ሚና ለመግለጽ የሚያገለግል አባባል ነው። በዘመናችን በመላው ዓለም የሚገኙ ዜጎች እነዚህን ተቋማት በመመስረት ስፍር ቁጥር የሌላቸው ተግባራትን እያከናወኑ ይገኛሉ። ለማንነታቸው መገለጫም ሆነዋል። የሙያና የሰራተኛ ማህበራት፣ ራስ አገዝ ቡድኖችና ማሕበራዊ ንቅናቄዎች፣ የሰብአዊ መብት ተሟጎቾች፣ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች፣ ወዘተ.... ትክ የለሽ አገልግሎታቸውን በማበርከታቸው የየአገራቱን መፃኢ እድል ብሩህ ማድረግ ችለዋል። በአገራችን ያለው የሲቪል ማሕበራት እንቅስቃሴስ ምን ይመስላል? ብለን ልንጠይቅ ይገባናል።

የሲቪል ማህበራት መደራጀት ጽንሰ ኃሳብ የፈለቀው በ18ኛውና በ19ኛው መቶ ክ/ዘመን አካባቢ እንደሆነ የሚገመት ሲሆን አደረጃጀቱና የፍልስፍና መሰረቱም እንደየአገራቱ ነባራዊ ሁኔታ የተለያየ ይዘትና ቅርጽ ነበረው። የማህበራዊ ሳይንስ ጠበብቱም ከልማትና እድገት ጋር በተያያዘ ተቋማቱ የሚፈጥሩትን የሲቪል ባህል የሚተነትኑ ሲሆን በኢትዮጵያም ልማዳዊ በሆነ መንገድ መደራጀት የጀመሩበት ጊዜ በርካታ ዘመናትን ያሳለፈ እንደሆነ ይገመታል። ሚናቸውም ምጣኔ ሃብታዊ እና ማሕበራዊ ችግሮችን የመፍታት ነበር። ዛሬ ሲቪል ማሕበራትና ዴሞክራሲ፣ ሲቪል ማሕበራትና ልማት፣ ሲቪል ማሕበራትና ማህበራዊ ደህንነት ተሳስረው የሚጓዙበት የዘመን ምዕራፍ ላይ እንገኛለን። ተቋማቱ እነማናቸው? የአደረጃጀታቸው ማዕቀፍና ሚናቸው ምንድነው? የዴሞክራሲ ስኬት ትምክህት ነው የሚያሰኝ ጠንካራ ተሳትፏቸውስ እንዴት ይለካል?

የሲቪል ማህበራት የዜጎች ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች አሳስበዋቸው በህጋዊ መንገድ የሚደራጁ፤ ከመንግስት ጣልቃ ገብነት ፈጽሞ የፀዱና የተወሰኑት ለብዙዎች የሚያበረክቱት የበጐ አገልግሎት ሰጪ ግለሰቦች ስብስብ ተቋም ነው:: ይህ ተቋም በዴሞክራሲያዊ ስርአት ውስጥ ዜጎች በግለሰብ ደረጃ ባላቸው  ነፃ ምርጫና ፈቃድ የማህበረ-ምጣኔ ሃብታዊና ፖለቲካዊ  ክህሎታቸውን እና አቋማቸውን እንዲያራምዱ እድሉን ይፈጥርላቸዋል:: በዚህም፤ በሰብአዊ መብት መከበር፣ በአካባቢ ጥበቃ፣ በህግ የበላይነት፣ በእምነት ተቋማት መቻቻል፣ በወጣት የልማት ማህበራት፣ በረድኤት ተግባራትና በመሳሰሉት አይነተኛ ሚናቸውን ይወጣሉ:: ከእነዚህ የሲቪል ማህበራት የተወሰኑት ያሉበት ምህዳራዊ ሁኔታና የሚጠበቅባቸው ኃላፊነት አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱ በግልጽ እየታየ ሲሆን ሜዳው አልጋ በአልጋ የሆነላቸው አስተኔ/ቅርጽ እንጂ ተፈላጊው ይዘትና አቋም የሌላቸው/        የሲቪል ማህበራት ደግሞ ተቋማቱ ከሚጠበቅባቸው የአሰራር ማዕቀፍ በተቃራኒ እየተጓዙ ይገኛሉ:: - ይህም አሳሳቢ ነው::

አሳሳቢ የሆነው ለምንድነው? አሳሳቢ የሚሆነው የሲቪል ማህበራት አደረጃጀት አላማ የመጨረሻ ግብ «ማህበራዊ ችግሮችን መፍታት» የሚል ሲሆን ይህ የሚሳካውም በባህርያዊ አፈጣጠራቸው መሰረት በነፃና በከፍተኛ ተሳትፎ ሕብረተሰቡን ያገለገሉ እንደሆነ ብቻ ሲሆን እየተመለከትን ያለነው ግን ከዚህ  በእጅጉ ፈቀቅ ያለ በመሆኑ ነው:: አሳሳቢ የሚሆነው ለሰብአዊ መብት እንሟገታለን የሚሉ ተቋማት በተዛባ ስሌት እንዲዳከሙ ተደርገው ለማህበረሰቡ መንፈሳዊ ልእልና የሚያደርጉት ተጋድሎ እንዲሸበብ ሲደረግና ብሔራዊ አጋርነታቸው ሲታጠፍ ነው:: ወይም በእንባ ጠራጊነትና በመብት ተቆርቋሪነት ጥላ ስር ሆነው ተግባራቸው ግን በሪፖርት መሰብሰብና የአልቃሽ ሙሾ አውራጅነት ሚና መጫወት ብቻ እንዲሆን ለራሳቸው ወሰን የቀረሩ እንደሆን የሚያስከትለው የሁለትዮሽ መዘዝ ነው::

ለሰብአዊ መብት መከበር የሚንቀሳቀሱ ተቋማት ግብ ዜጎች መብቶቻቸውን በማወቅ ለማስከበር የሚያስችላቸውን የሲቪክ፣ የዴሞክራሲና የሰብአዊ መብት ትምህርቶች (ቅስቀሳዎች) በመስጠት ለመብቱ የሚቆረቆር ማህበረሰብ መፍጠር ነው:: ይህም ልማት የሚረጋገጥበትን መሰረታዊ ቁልፍ በመጨበጥ የዴሞክራሲ ስርአትን ይገነባል:: ሁለት ችግሮች ግን በዚህ መስመር ላይ እንዳንጓዝ መሰናክል የሆኑብን ይመስላል::

የመጀመሪያው የሲቪል ማህበራትና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ህግ በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት አማካይነት ከፀደቀ በኋላ የተከሰተው ድብርታ (gloominess) ነው:: ይህ ህግ ስቪክ ማህበራትና ተራድኦ ድርጅቶች ከ10 በመቶ በላይ ከውጭ ድጋፍ እንዳያገኙ በዚህም ሚናቸውን እንዳይወጡ ያሽመደመደበት ስሌት ነው:: ይህ የሆነበት ምክንያት ሌሎች ግንዛቤዎች ተወስደውም ሊሆን ይችላል:: ይሁንና ህጉ ከፀደቀ በኋላ በአገር ውስጥ ያሉና ይበልጡን በዓለም አቀፍ የሰብአዊ ተቋማትና ግለሰቦች በመረዳት ተግባራቸውን ሲያከናወኑ

ከቆዩት ድርጅቶች አብዛኞቹ እየተዳከሙ የሄዱበት ሁኔታ ተፈጥሯል:: ሚናቸው በእጅጉ እየተገደበ ለሰብአዊ መብትና ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ቀንሷል:: «በአፍራሽ ተግባር ላይ ተሰማርተው ነበር ብለን ጣታችንን የቀሰርንባቸው አሉ» ከተባለም ጉዳዩ «ከኑግ ጋር የተገኘሽ መጭ...» በሚል ስሌት ሁሉንም መረምረም ይሆናል:: ፍትሃዊ አይሆንም:: - አይደለም::

ከሌሎች አገራት ገንቢ ተሞክሮዎችን መቅሰም ከፈለግን «ሌሎች» ለሲቪል ማሕበራት ያላቸውን ግምትና አክብሮት እንመለከታለን:: እኛም ያስፈልጉናል:: ያስፈልጉናል ስንል ግን በሁለተኛ መሰናክልነት የተቀመጡትን የችግር መንስኤ የሆኑ ማሕበራት/አስተኔዎቹን/ አይነት አይደለም::

መሰረታዊ የልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ቁልፍ የሆነው የስብዕና ክብር መረጋገጥ እውን እንዳይሆን የዴሞክራሲ ስርአት መገለጫ የሆኑት ሃሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት በስልታዊ አካሄድ እንዲገታ፣ ነፃና ርትአዊ የፖለቲካ ምርጫዎች እንዳይከናወኑ ላይ ታች የሚሉ ያጋጥማሉ:: እነዚህ ተቋማት ከሲቪል ማህበራት የነጻ አደረጃጀት ባህሪ አፈንግጠው የሚጓዙ፤ የቱንም ያህል የገቢ አጠቃቀም ህግ ቢወጣ ካዝናቸው ስለማይጐድል አሉታዊ ጫናቸውን እያሳረፉ የሚቀጥሉ ናቸው:: የመልካም አስተዳደርና የፍትህ እጦት ህዝቡን አሳር በሚያሳይበትና ሰው ሰራሽ ማህበረሰባዊ መፈናቀሎች በየዕለቱ በሚያጋጥሙበት ሁኔታ ምን እየሰሩ ነው? በአገር አቀፍ ምርጫ ክንውን ዋዜማ ላይ ሆነን ህጋዊ የፖለቲካ ፓርቲነት ፈቃድ አላቸው ስለሚባሉት ተፎካካሪዎች የሚሰጡት የፍትሃዊነት ሽፋን ምን ይመስላል? እንባ ጠራጊዎች ናቸው ወይስ የአልቃሽ ሙሾ አውራጆች? መመለስ ይኖርበታል::

የእንባ ጠራጊ ማሕበራት መገለጫ ፍትሃዊነትና ማህበረሰባዊ ችግር ፈችነት ነው:: በጋራ ፍላጐት ዙሪያ መስራት፣ ሰብአዊ ልእልናን ማረጋገጥና ማህበረሰቡ ዋጋ የሚሰጣቸውን እሴቶች መንከባከብ ነው:: በቅርቡ ደግሞ የግጭት ፈቺነት ተግባራትን የሚያከናውኑት አይነተኛ ሚና በዓለም አቀፍ ደረጃ እየተጎናፀፉ ሄደዋል:: በአገራችንም ያላስፈላጊ ግጭቶች እየቀሰቀሱ አቅጣጫቸው በግልጽ ወዳልታወቀ አሳሳቢ ሁነቶች እየተጓዙ ነው:: ዜጎች ለአመታት ከኖሩባቸው አካባቢዎች ይፈናቀላሉ:: መብታቸው ይረገጣል፣ ንብረታቸው ይዘረፋል:: ከዚያ «የሚመለከታቸው የህግ አካላት» መፍትሄ ማፈላለግ ይጀምራሉ:: ህጋዊና ባህላዊ መፍትሄዎች በአይነት ይሞከራሉ:: የሲቪል ማህበራት ሚና ግን ዋጋ የተሰጠው አይመስልም:: የማህበራዊ ሳይንስ ተመራማሪዎች ለግጭት አወጋገድ (conflict resolution) የሲቪል ማህበራት የሚጠናከሩባቸውን ፖሊሲ ዎችና ህጎች ማወጣት የሚክስ ተግባር መሆኑን ይመክራሉ:: ማህበራቱ ከህዝቡ ይመነጫሉ፣ ለህዝቡ ነፃ

አገልግሎታቸውን ያበረክታሉ በዚህም ተደማምጠው የጋራ አቋም መያዝ ይችላሉ:: ገንቢና ሊኮረጅ የሚገባው ነው::

በሌላ በኩል የአፍራሽነት ሚና ሊኖራቸው ይችላል ተብሎ ለሚታሰቡ ፖሊሲ በመቅረጽ በነባራዊ የአሰራር ህግ መቆጣጠር ይቻላል:: ያሉትን ችግሮች ከመፍታት ይልቅ አንደኛውን ወገን በሚጠቅም መልኩ በሌሎች ላይ ስውር ጥቃት የሚከፍቱ አስተኔ የሲቪል ማህበራት ደግሞ የአልቃሽ ሙሾ አውራጅ ተግባራቸውን ካላቆሙ/ችግሩን በማባባስ/ የሁለትዮሽ ጉዳቱ ለአገር መትረፉ አይቀርም::ያሳስበናል የምንለውም ይህንን ነው:: ይህ ችግር ደግሞ ለአገር አቀፍ ምርጫ በወራት የሚቆጠሩ ጊዜያት በቀሩበት ወቅት እንኳ እየተመለከትን ነው:: በዚህ ወቅት በምርጫ ትምህርትና በሲቪክ አድቮኬሲ ላይ እንሰራለን፣ ለሰብአዊ መብት መከበር እንታገላለን የሚሉ ተቋማት ማንነት ችግር ፈቺዎች ወይስ ችግር አባባሾች በሚል የሚፈተሹበት ነው:: ሊፈተሹ ይገባቸዋል::

በየትኛውም የዓለም ክፍል አገር አቀፍ ምርጫ ሲካሄድ ምርጫው ሁሉን አቀፍ፣ ነፃና ርትአዊ፣ ምስጢራዊ የአመራረጥ አፈፃፀም እንዲኖረውና በመሳሰሉት ዙሪያ በምርጫ ላይ እንሰራለን የሚሉ ወገኖች ከወገንተኝነት የፀዳ የሌት ተቀን ሥራቸውን ያከናውናሉ:: የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርቶችንና እንቅስቃሴዎችን ባሉት መንገዶች (Chanals)ሁሉ በማስተላለፍ ኃላፊነታቸውን ይወጣሉ:: አቋማቸው ሚዛናዊ፣ የውሳኔ መነሻቸው ፍትሃዊና ርትአዊ ብቻ መሆን አለበት::

በቅርቡ ገዢው ፓርቲን ጨምሮ ሌሎች ተፎካካሪ ፓርቲዎች እየተደራደሩ እንደነበር ይታወሳል:: የዴሞክራሲ ስርአት መገንባት ግድ እስከሆነ ድረስ ደግሞ ውይይቶች፣ ድርድሮች ይቀጥላሉ:: ሊቀጥሉ ይገባቸዋልም::ይህ በሚሆንበት ወቅት ሁሉ ደግሞ፤ በዴሞክራሲያዊ መንገድ ቅድመ ሁኔታዎችን ከማስቀመጥ አንስቶ ድርድር አቋርጦ እስከመውጣት ያሉ እርምጃዎች ሊወሰዱ ይችላሉ:: የፖለቲካ ድርጅቶቹ ይህን እርምጃ ሲወስዱ ውሳኔያቸው በቀጣይ ሂደት የሚያጎናጽፋቸው የበላይነት ወይም ጊዜያዊ ኪሳራ ሊኖር ይችላል:: ሰሞኑን እየተደረገ በነበረው ተመሳሳይ ድርድርም «መድረክ» የተሰኘው የፓርቲዎችና የግለሰቦች ስብስብ ድርድሩን አቋርጦ የወጣበት ተሞክሮ አለ::

ድርድር በፖለቲካ ስርአት ውስጥ በተለያዩ ጊዜያት የሚደረግ ጠንካራ ጐኖች የሚጐለብቱበት ከስህተቶች እርማት በመውሰድ የላቁ እመርታዎች የሚጨበጡበት ነው ብለን እናምናለን:: ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ግን በአገር በቀልነት ስም የአፍሪካዊነት ተሞክሮ ካባ ጭምር ለብሰናል የሚሉ የሲቪል ማህበር ተብዬዎች እርምጃውን በማጥላላት ጉዳዩን ለህዝብ ያቀረቡበት መንገድ ሊታረም የሚገባው ነው:: ስብስቡ ድርድሩን ስላቋረጠበት ምክንያት ፍትሃዊ ምርመራ በማድረግ አስተማሪ መልዕክት ማስተላለፍ ሲቻል ተጠሪነቱን ለማሳየት በሚመስል መንገድ ትችቱን ደርድሯል:: ሲቪል ማህበራት ይደርጁ ስንል በሲቪል

ማህበርነት ስም የአሉታ ካባ የተጀቦኑ ይኑሩ ማለታችን አይደለም፡፡ ህዝቡ በጥንቃቄ ሊፈትሻቸው ይገባል፡፡ ነን የሚሉትን ሳይሆን የሚያደርጉትን መመርመር ያስፈልጋል፡፡ ቢቻል የግንባታው አካል መሆን ካልተቻለ ግን አርፎ መቀመጥ ‹ጨዋነት› ነው፡፡በአገራችን ሲቪል ማህበራት ተጠናክረው የችግር ፈቺነት ሚናቸውን በአግባቡ እንዲወጡ፣በኢኮኖሚያዊ፣ማህበራዊና ፖለቲካዊ ዘርፎች አገዛቸውን እንዲያበረክቱ እንመኛ ለን፡፡በበርካታ ዓለማት በተቋማቱ እየተከናወነ ያለው የግጭት አስወጋጅነት በጎ ተሞክሮ ተመሳሳይ ችግር በተደጋጋሚ እየጎበኘን ላለነው ህዝቦችም በአርአያነቱ እንዲተገበር የግድ ይላል-አቅማችን በፈቀደ መጠንም ተሳታፊ ለመሆን ቃል እንገባለን፡፡

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!

# Verbatim

«እንኳን ከኦባማ ጋር፣ ከፀሃይ በታች ካለ ከምንም ነገር ጋር በማንስማማበት ወቅት አለመስማማታችንን በፋይ እንገልጻለን! እንገልፃለን፡፡ ያ በየወቅቱ የውጥረት ስሜት ይፈጥራልን? አዎ ምናልባት ሊፈጥር ይችላል፡፡»

አቶ መለስ ዜናዊ

የኢፌዲሪ ጠ/ሚኒስትር

**በአሁኑ ወቅት ያለው የኢትዮ-አሜሪካ ግንኙነት ምን እንደሚመስል ተጠይቀው የሰጡት ምላሽ**

«ከዚህ ውስጥ መድረክ በራሱ ምክንያት ከድርድሩ ወጥቷል፡፡አሁን ደግሞ አደራዳሪዎች እስከ ሰኞ ጠብቋቸው ብለው ጠይቀውናል፡፡ እኛም እስከ ሰኞ (ድርድሩን) አቋርጠን እየጠበቅናቸው ነው፡፡»

ኢ/ር ኃይሉ ሻውል

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (የመኢአድ) ፕሬዝዳንት/

**በኢህአዴግና በተቃዋሚዎች መካከል እየተካሄደ ያለው ድርድርና ስላለበት ሁኔታ ከፍትህ ጋዜጣ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ**

«...ችግሮች አሉ ብለን ስለምናምን ነው በቅድሚያ ከኢህአዴግ ጋር መደራደር አለብን የምንለው:: ለድርድሩ በገዢው ፓርቲ በጎ ፈቃዱ ከተገኘ ችግሮቹን ተወያይቶ መፍታት ይቻላል::»

አቶ ጉዕሽ ገብረስላሴ

«የመድረክ» የወቅቱ ሊቀ መንበር/

**በመጪው ምርጫ ለመሳተፍ አመቺ ሁኔታ አለ ወይ ? በሚል ከሪፖርተር ጋዜጣ ተጠይቀው ሲመልሱ**

# ዜናዎች

# ቴዲ አፍሮ:- በአዲስ አበባ ስታዲየም የመጀመሪያውን ታላቅ ኮንሰርት ከሳምንት በኋላ ያቀርባል

## ከሲያትልና ቺካጎ በሚመጡ ሙዚቀኞች ዝግጅቱ ይደምቃል

# ገቢው ለችግረኞች መርጃ ይውላል

ድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ) ዛሬ ከሰዓት በኢንተርኮንቲኔንታል ሆቴል በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ጥቅምት 1 ቀን 2002 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ስታዲየም የሙዚቃ ኮንሰርት እንደሚያቀርብ አስታወቀ።

ድምጻዊው በመግለጫው ላይ ኮንሰርቱን ያዘጋጀው ችግረኞችን ለመርዳት እንደሆነ የገለጸ ሲሆን «ኤልሻዳይ» ከተሰኘ በጎ አድራጎት ድርጅት ጋር በመነጋገር ጥቅምት 1 ቀን 2002 ዓ.ም በአዲስ አበባ ስታዲየም በሚካሄደው በዚህ የሙዚቃ ኮንሰርት ከትኬት የሚገኘው ገቢ ሙሉ ለሙሉ ከተለያዩ ክልሎች ፈልሰው አዲስ አበባ ውስጥ በልመና ላይ ለሚገኙ ችግረኞች እንደሚውል ተናግሯል። ቴዲ በመጀመሪያ የአበበች ጉበና ህፃናት መርጃን መርዳት ፍላጐት እንደነበረው ገልጾ፤ የአበበች ጉበና ድርጅት በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ራሱን ስለቻለ «ኤልሻዳይ» ከተባለው በጐ አድራጐት ድርጅት ጋር በመነጋገር ቅድሚያ ጉዳና ላይ ላሉት ወገኖች ልንደርስላቸው ስለሚገባ ይህንን ውሳኔ ወስኛለሁ ብሏል።

«መቼም ኮንሰርት ላይ ብቻህን አትዘፍንም፤ አብረውህ የሚጫወቱ ድምፃውያን መርጠሀል ወይ? ከመረጥክስ እነማን ናቸው?» ተብሎ ከአውራአምባ ታይምስ ለቀረበለት ጥያቄ ቴዲ ሲመልስ «እርግጥ አብረውኝ የሚጫወቱ ሙዚቀኞች አሉ። እነሱም ከችጋጉ እና ከሲያትል የሚመጡ ሲሆን ጠቅላላ ወጪያቸውን የምሸፍነው እኔ ራሴ ነኝ።» ካለ በኋላ «የድምጽ እና የሙዚቃ መሳሪያውን ማስተባበሩን እና መድረክ መምራቱን እንዲሁም ኮንሰርቱ በተሳካ ሁኔታ እንዲካሄድ ለሚያስፈልጉን ወጪዎች ስፖንሰሮችን ለማፈላለግ አዲካ እና ኤም.ጂ ለተባሉ ድርጅቶች ሙሉ ኃላፊነቱን ሰጥቻለሁ» ብሏል።

ከቃሊቲ የአንድ አመት ከአራት ወር የእስር ቆይታው በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚዘጋጀው ይህ የሙዚቃ ኮንሰርት የመጨረሻው እና ትንሹ የመግቢያ ትኬት ዋጋ 10 ብር እንደሆነ የተናገረው ቴዲ አፍሮ ከፍተኛ የሚባለውን ዋጋ ለጊዜው እንደማያውቀው ቢናገርም አንዳንድ ምንጮች ግን ክቡር ትሪቡን 200 ብር እንደሚያስከፍል እየገለጹ ነው። እንዲህ አይነቱ የበጐ አድራጐት ተግባር ለማከናወን መቼና እንዴት እንዳቀደም ከጋዜጠኞች ጥያቄ ቀርቦለት ሲመልስ «እኔ ሁሌም በጐ ነገር ለማድረግ እመኛለሁ። ወደፊትም ህይወቴ እስከቀጠለ ድረስ ይህ በጐ ሥራ ይቀጥላል።» ብሏል ።

ቴዎድሮስ ካሳሁን ጋዜጣዊ መግለጫ በሰጠበት ወቅት በውስጡ መረጋጋትና የደስተኝነት ስሜት ይንፀባረቅበት የነበረ ሲሆን የውጭ አገር ጋዜጠኞች የተናገረውን በእንግሊዝኛ እንዲደግምላቸው በጠየቁት ጊዜ «በእንግሊዝኛ ከፈለጋችሁ በግል አናግሩኝ

አሁን ግን መናገር የምፈልገው በአማርኛ ብቻ ነው» ብሎ ንግግሩን በአማርኛ ከጨረሰ በኋላ ለውጭ ጋዜጠኞች መጨረሻ ላይ መግለጫውን በእንግሊዝኛ ሰጥቷል፡፡

ቴዲ መግለጫውን የሰጠው በማናጀሩ በአቶ አዲሱ ገሰሰ ታጅቦ ሲሆን ማናጀሩ አቶ አዲሱ ገሰሰ ድምጻዊው መግለጫውን ለመስጠት ቦታውን ከመያዙ በፊት ጋዜጠኞች በኮንሰርቱና በኮንሰርቱ ዙርያ ብቻ ጥያቄ በማንሳት እንዲተባበሯቸው አደራ ያሉ ቢሆንም ጋዜጠኞች ግን ከኮንሰርቱ ጋር ተያያዥነት የሌላቸው ጥያቄዎችን ከመጠየቅ አልቦዘኑም፡፡ ቴዲም «ከአጀንዳ ውጪ ቢሆንም ልመልስ» በማለት በፈገግታ እየታጀበ ምላሽ ሰጥቷል፡፡ ቴዲ አያይዞም ለዚህ ለተቀደሰ አላማ ሁሉም ባለሀብቶች አጋር እንዲሆኑና እጃቸውን እንዲዘረጉ አደራ ብሏል፡፡

በአርቲስት ጥላሁን ገሰሰ የቀብር ስነ-ስርዓት ላይ አልተገኘህም በዚህስ ምን ተሰማህ? በኮንሰርቱ ላይስ ስለ ጥላሁን ምን ለማድረግ አስበሃል የሚል ተጨማሪ ጥያቄም ተነስቶ ነበር፡፡ «እውነት ለመናገር በጥላሁን ገሰሰ ሞት የተሰማኝ ጥልቅ ሀዘን ምን ያህል እንደሆነ ከዚህ በፊትም ተናግሬያለሁ አሁንም በድጋሚ ለመግለጽ እወዳለሁ፡፡» በማለት የተናገረው ቴዲ በኮንሰርቱ ላይ በተወሰነ ደረጃ ጥላሁን ገሰሰ የሚታወስበት ሁኔታ ይኖራል ይህም የዝግጅቱ አንድ አካል ነው ሲል ምላሽ የሰጠ ሲሆን በዚህ የሙዚቃ ኮንሰርት ላይ በመገኘት እና ትኬት በመግዛት ለወገኖቻችን እገዛ እናድርግ በማለት ጥሪ ከማስተላለፍ ውጪ ለጥያቄው ምላሽ ከመስጠት ተቆጥቧል፡፡ «ማንኛውንም ስራ ለማስራት ችሎታ ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ ፍፁም ቅንነትም ያሻል፡፡» በማለት ከቅንነት የሚገኘውን ውጤት በኩራት ያሰመረበት ቴዲ፡፡ የሙዚቃ ኮንሰርቱን ለጐዳና ተዳዳሪዎች ባደርግም በግሌ ግን የአበበች ጐበና ህፃናት መርጃ ድርጅትን ለመርዳት ዝግጁ ነኝ ብሏል «ኤልሻዳይ» የተሰኘው በጐ አድራጐት ድርጅት ከዚህ ቀደም ከክልል እየፈለሱ ከመጡትና በልመና ከሚተዳደሩት ውስጥ 28ሺህ ያህሉን ወደ ቀያቸው እንዲመለሱና እንዲቋቋሙ ያደረገ ሲሆን አሁንም ከመቶ ሺህ በላይ በልመና የሚተዳደሩ በከተማችን ውስጥ ስላሉ ጥቅምት አንድ የምናካሂደው የሙዚቃ ኮንሰርትና ከዝግጅቱ የሚገኘው ገቢ የተወሰኑትን ይረዳል ይህም እንደዜጋ የሚያስደስት ነው ወደፊትም እንደዚህ አይነት በጐ አድራጐቶች ሊበረታቱ ይገባል ብሏል፡፡

ቴዲ በመጨረሻም የሙዚቃ ኮንሰርቱ በጥሩ ሁኔታ እንደሚጠናቀቅና ገቢውም በችግር ላይ ላሉ ወገኖቻችን መጠነኛ እገዛ እንደሚያደርግ እምነቴ ነው ሲል ንግግሩን በምስጋና ቋጭቷል፡፡

# በሚድሮክ ስር የሚገኝ ፋብሪካ በሚለቀው መርዛማ ዝቃጭ አካባቢው እየተበከለ ነው

**« በኢንቨስተሮች መካከል በሚደረገው የሕግ ጥበቃ መካከል ልዩነት መደረግ አለበት?»**

**አቶ ተፈራ ሙላት**

የሚድሮክ እህት ኩባንያ የሆነውና ሳራ አምፑልን የሚያመርተው ዴይላይት ኢንጂነሪንግ ፋብሪካ በሚለቀው ዝቃጭ (Waste Product) ህጋዊ የኢንቨስትመንት ፈቃድ አውጥቼ የሚካሄደውን የከብት እርባታ ፕሮጀክት ከፍተኛ ኪሳራ እንዲደርስበት አድርጓል ሲሉ በግል የኢንቨስትመንት ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩት አቶ ተፈራ ሙላት ቅሬታቸውን ለዝግጅት ክፍላችን ገለፁ፡፡

በየካ ክ/ከተማ ቀበሌ 20/21 የካ አባዶ የካ ጣፎ አስተዳደር ውስጥ ለሚያካሂዱት የከብት እርባታ ኢንቨስትመንት በኢፌዴሪ የአዲስ አበባ አስተዳደር ንግድ ኢንዱስትሪና ቱሪዝም ቢሮ በምዝገባ ቁጥር አአ.3/ግን-7-11747/93 ፈቃድ በማውጣት ከ1993 ዓ.ም ጀምሮ ራሳቸውን ከመጥቀም አልፈው ለበርካታ ዜጎች የሥራ እድል መፍጠራቸውን ያስታውሱት አቶ ተፈራ አሁን የተፈጠረው ችግር ግን ልማታዊ እንቅስቃሴውን እያደናቀፈው መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ «ከ200 ሺህ ብር በላይ ውጪ በማድረግና የውሃ ግድብ በማሰራት ያዘጋጀኑው የእንስሳት ውሃ መጠጫ ከፋብሪካው በሚለቀቅ ዝቃጭ በመበከሉ አስራሶስት የቁም ከብቶች አልቀዋል፡፡ ኢንቨስትመንት መጠኑ ሊለያይ ይችላል፤መዋእለ ንዋያቸውን ፈሰስ ባደረጉ ሁለት ባለሃብቶች መካከል የሚደረገው የህግ ጥበቃ ግን እኩል መሆን ነበረበት፡፡ » ሲሉ ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡ ጉዳዮን አስመልክቶ ለቀበሌው አስተዳደር ተደጋጋሚ አቤቱታ ባቀርብም ምላሽ ተነፍጌያለሁ ብለዋል፡፡ ከክ/ከተማው የአካባቢ ጥበቃ ያገኙት ምላሽም ለችግሩ ትኩረት እንዳልተሰጠው የሚያሳይ በመሆኑ የሚመለከታቸው አካላት መፍጥሄ እንዲሰጡበት ጠይቀዋል፡፡

ባለሃብቱ ያቀረቡትን ቅሬታ አስመልክቶ በትናንትናው እለት በየካ ጣፎ አስተዳደር ውስጥ በሚገኘው የዴይላይት ኢንጂነሪንግ ፋብሪካ በመገኘት የድርጅቱን አስተዳደር አስተያየት ለማካተት ብንሞክርም ሃላፊዎቹ ስብሰባ ላይ ናቸው በመባሉ ሊሳካልን ያለመቻሉን እንገልፃለን፡፡

# የሙዚቃው ንጉሥ 69 ዓመት ልደት ተከበረ

## ቴዲ ለመጀመርያ ጊዜ በመድረኩ ላይ አቀነቀነ

**በአቤል ዓለማየሁ**

- **«የጥላሁንን ያህል ማን ለሀገሩ ሰርቷል?» 55 ዓመት ተምሯል፣ አስተምሯል፤ የተሰጠው የክብር ዶክትሬት ያንሰዋል እንጂ አይበዛበትም»**
- **«ድምፁን ለማሻሻል ሰዓት ይዞ ገንዳ ውስጥ የሚያሳልፍ ሰው ነው:: ይህን አሁን ስንቶቻችን እናደርጋለን?»**
- **«ሥራዎቹ ተሰብስበው በእጃችን ባለመኖራቸው መጪው ትውልድ ቢጠይቅ ስለ ጥላሁን የምናቀርበው የለንም::»**

*ሀገሩና ህዝቡን ያላነሳበት መድረክ የለም:: ለኢትዮጵያና ለህዝቧ ያለውን ፍቅር መግለጽ ሲጀምር እንባ ይቀድመዋል:: ያልዘፈነበትን ርዕስ መፈለግ ጊዜ እንደ መጨረስ ይቆጠራል:: በረሀብ አለንጋ የተገረፉ ወገኖችን ለመታደግ፣ በጦርነት መድረክ የጠላትን ኃይል ለማንበርከክ የተሰለፉ የሠራዊት አባላትን ለማበረታታት ጀግኖ ያጀገነ፤ ጀግና ነው:: በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት በእጅጉ ታሞ የነበረ ቢሆንም በምሽግ ከነበሩ ወታደሮች አልነጠል ብሎ አስቸግሮ በልመና ጉርጓዱን ተሻግሯል:: በከፍተኛ ጣሪያም ሆነ በዝቅተኛ ደረጃ የሚያወጣቸው ድምጾች ሳይሰለቹና ሳይጠገቡ እንደ ጅረት ከግማሽ ክ/ዘመን በላይ ፈሰዋል:: አፈሩ የጠራው ይመስል ህክምና ያደርግ ከነበረበት አሜሪካ ወደ ሀገሩ በገባበት ያለፈው ዓመት በዓለ ትንሣኤ «መጣ» ሳይሆን «አረፈ» የሚለው ዜና ቀድሞ ተሰማ:: የቀብር ሥነ-ሥርዓቱ የሰው ነጭ የታየበት ነበር:: «ይህንን ዳግመኛ ማን ይታደለዋል?» ያስባለም ጭምር:: በህይወት እያለ ከተሰጠው ክብር በበለጠ በሞቱ ቢነግስም ታላቅነቱን ትላንት፣ ዛሬም፣ ነገም ስራዎቹ አፍ አውጥተው የመናገር ያህል አቅም አላቸው፤ ስለ ህያዉ የሙዚቃ ንጉስ ዶ/ር አርቲስት ጥላሁን ገሠሠ::*

*በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ በሚከበረው በዕለተ መስቀል መስከረም 17-1933 ዓ.ም. የተወለደው አርቲስት ጥላሁን ገሠሠ 69ኛ የልደት በዓል ቤተሰቦቹ፣ የሙያ ጓደኞቹና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በተገኙበት እሁድ ማምሻውን በሒልተን ሆቴል ተከብሮ አምሽቷል::*

*ከጥላሁን ህልፈት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ የተከበረው የልደት በዓሉ የተጀመረው በአንድ ደቂቃ የህሊና ፀሎት ነበር:: ከዚያም ከ55 ዓመት በላይ ለጥበብ ለከፈለው ከፍተኛ መስዋዕትነትና ለዋለው ተነግሮ የማያልቅ ውለታ የሰላሳ ሰከንድ የአድናቆት ጭብጨባ ፎቶው ከፍ ብሎ በአዳራሹ እየታየ ተደረገለት::*

*«ጥላ ከለላዬ» ጥላሁን ገሠሠ ለመጀመሪያ ጊዜ የሀገር ፍቅርን መድረክ ሲረግጥ የተጫወተው ዜማ ነው:: ይህን ዜማ ሲያንቆረቁር ወደ ፊት በሙሉ ድምጽ «የኢትዮጵያ የዘመናዊ ሙዚቃ ንጉሥ» ተብሎ ስሙ ከዳር እስከ ዳር ይገናል ብሎ የገመተ ባይኖርም*

ጆሮ ሊሰጠው የሚገባ ድምፃዊ እንደሆነ ግን ያሳየበት ነበር:: የሙዚቃው ደራሲ ኢዮሔል ዮሐንስ ነበሩ::

**«ጥላ ከለላዬ ኢትዮጵያ አገሬ**

**ኩራት ተሰምቶኛል ካንቺ መፈጠሬ»**

የሚል ስንኝ የተካተተበትን ይህን ዜማ የሦስት ትውልድ አባላት በጋራ በመድረክ ላይ በመጫወት «ህያዉ»ን አርቲስት ዘክረውታል::

«ታላቅ ቅርስና ሀብት» ያሉት የባህልና ቱሪዝም ሚኒስትር መልዕክተኛ ዶ/ር ሰለሞን አሊ፣ ሚኒስትር ሙሐመድ ድሪርን ወክለው የተገኙት ለስራ ከከተማ በመውጣታቸው ምክንያት መሆኑን ገልፀው ጥላሁን በሙያው ለሀገሩ ካበረከተው ከፍተኛ አስተዋፅኦ አንፃር ብዙ ሊደረግለት እንደሚገባ አውስተዋል::

የአንጋፋው አርቲስት ተስፋዬ አበበ (ፋዘር) ተማሪዎች በህብረት «የጥበብ አርበኛው» ሲሉ ሽለላና ፉከራ እንዲሁም ታላቅነቱን የሚዘክር ዜማ በተመስጦ ሲከታተላቸው ለነበረው ታዳሚ አቅርበው በሞቀ ጭብጨባ ተሸኙና ተራው የጌትነት ሆነ::

አርቲስት ጌትነት እንየው ከዘጠኝ ዓመት በፊት የጥላሁን 60ኛ ዓመት በደመቀ ሁኔታ ሲከበር ያቀረበውንና «እውቀትን ፍለጋ» ከሚለው የግጥም መድብሉ ላይ የካተተውን «ቃል ህይወት - ህይወት ቃል» የሚለውን አርቲስቱን የሚያወድስ ግጥም አንብቧል::

**«ጥላሁን ሀገር ነው»**

«የጥላሁን ሞት ብዙ ነገር አስተምሮናል» ሲሉ ንግግራቸውን የጀመሩት ባለቤቱ ወ/ሮ ሮማን በዙ «ጥላሁን ሀብቴ የኢትዮጵያ ህዝብ ነው ይል ነበር:: አስከሬኑ በተሸኘበት ጊዜ እውነታውን ተረድተናል::» ብለው ንግግራቸውን ሲቀጥሉ «ጥላሁን አንድ ሰው አይደለም፤ ሀገር እንጂ:: ያለቀሰለት ሀገር ነው:: ያዘነለት የአንድ ዘመን ትውልድ አይደለም:: መልከዓ-ምድራዊ አቀማመጥ ሳይወስነው ህዝብ አዝኖለታል::» ሲሉ በዓለም ላይ በብዙ ቦታዎች ሀዘናቸውን የገለፁ ስለመኖራቸው ጠቁመዋል::

«ጥላሁን በህይወት ቢኖር ኖሮ በእልልታና በጭብጨባ ልደቱን እናከብርለት ነበር፣» በማለት ንግግራቸውን የቀጠሉት ወይዘሮዋ «በአፀደ ስጋ ቢለየንም ስራውና ራዕዩ አብሮን ይኖራል:: ሥራዎቹ ተሰብስበው በእጃችን ባለመኖራቸው መጪው ትውልድ ቢጠይቅ ስለ ጥላሁን የምናቀርበው የለንም:: የተሰባሰበ፣ እሱነቱን የሚገልጽ ሰነድ የለውም:: እኛን አገለገለ እንጂ ያደረግንለት ምንም ነገር የለም:: ስራዎቹ ይሰብሰቡ፣ ገላጭ ፊልም ይሰራለት፣ መጽሐፉ ከሙት ዓመቱ በፊት ተጽፎ ይድረስለት::» ሲሉ ቅሬታና ማሳሰቢያ

አሰምተዋል:: በዋናነትም የስኳር በሽተኞች የህክምና ማዕከል የማቋቋም ፍላጐት እንደነበረው የሚታወቅ ሲሆን «እኔ ባልፍ እንኳን አንቺ እንድትሰሪው ብሎ ያስገባኝን ቃል ሁላችንም አደራ አለብንና እንቀበለው::» ሲሉ አደራውን አስተላልፈዋል::

### «መንግስትን እጁን መጠምዘዝ ያስፈልጋል»

ሀገራችን ጀግኖቿን በህይወት እያለ የሚያከብርላት ህዝብ፣ መሪና መንግስት የታደለች አትመስልም:: ከጥንት ዘመን አንስቶ የወፈረ ስም ታሪክና ስም አኑረው ላለፉ ጀብደኞች ሊታወሱበት የሚችል ቋሚ መጠሪያ ብዙ (ኧረ ጥቂትም) የላቸውም:: ጥላሁን ከሞተ በኋላ ያገኘውን ክብር በህይወት ዘመኑ ሳለም ማግኘት ይገባው እንደነበር ብዙዎች በቁጭት ይናገራሉ:: ምንም እንኳን የጥላሁንን ነፍስ ሀሴት እንድታደርግ አስተዋጽኦ ባይኖረውም አሁንም ቢሆን ህያው የሆነ መታሰቢያ እንዲሰራለት የሚሞግቱ ድምፆች በየጊዜው ይሰማል:: ወ/ሮ ሮማን «በልባችን ትልቅ ቦታ አለው» ላሉት ክቡር አርቲስት ጥላሁን ገሠሠ በየዓመቱ እንዘክርለታለን ካሉት የልደት ቀኑ በተጨማሪ የሙዚቃ ት/ቤትን መሰል ቋሚ ነገር እንዲሰየምለት ጠይቀዋል:: የዝግጅቱ መድረክ መሪ ኪሮስ ኃ/ሥላሴ ለጥላሁን ብዙ ነገር እንዲደረግ «መንግስትን እጁን መጠምዘዝ ያስፈልጋል» ሲል ጉትጎታ መኖር እንዳለበት ተናግሯል::

### መስከሩ...

አርቲስት አሰለፈች አሽኔ ጥላሁን ገሠሠን ከ14 ዓመት ዕድሜው ጀምሮ ታውቀዋለች:: በዝግጅቱ ላይ ምስክርነት ለመስጠት ከመድረክ ከተጋበዙ ሰዎች መካከልም አንዷ ነበረች:: «የጥላሁንን ያህል ማን ለሀገሩ ሰርቷል?» ስትል የጠየቀችው አሰለፈች የሙያ አጋሯን «55 ዓመት ተምሯል፣ አስተምሯል፤ የተሰጠው የክብር ዶክትሬት ያንሰዋል እንጂ አይበዛበትም» ያለች ሲሆን «ፀሀፍት ከጠየቁን ስለ ጥላሁን አንጋፋዎቹ ብዙ ነገሮችን ልንናገር፣ ልንመሰክር እንችላለን» ስትል በደራሲያን ማኅበር እየተፃፈ ለሚገኘው የጥላሁንን ታሪክ ለሚያትተው መጽሐፍ ጠቃሚ መረጃ መስጠት እንደምትችል ጠቁማለች::

የጥላሁንን ስራዎች የሚያሰባስበውና የአድናቆቱ መጠን ከልክ ያለፈ የሚመስለው የሀረሩ ነዋሪ ንጉሴ ታደሰ ጥላሁንን የሚያወድስ ንግግር ካደረገ በኋላ «ለስኳር ህመምተኞችና ለአረጋዊያን መጦሪያ የሚሆን ድርጅት መቋቋም ለነበረው ፍላጐት ይረዳው ዘንድ ሥራዎቼን ባሉበት መልኩ አሰርቼ ለህዝብ አድርሼ በማገኘው ገንዘብ ሥራውን እጀምራለሁ:: ከዚያ በኋላ የኢትዮጵያ ህዝብ እርዳኝ ብለው እምቢ አይለኝም» ሲል በእርሱና

በወ/ሮ ሮማን ፊት ተናግሮ እንደነበር በማውሳት ውጥኖቹ ምንም እንኳን እሱ በህይወት ኖሮ ባያያቸውም እንዲሳኩ መረባረብ የሁሉም ድርሻ ነው የሚል መልዕክቱን ካስተላለፈ በኋላ «ጥላሁንን ትላንትም፣ ዛሬም፣ ነገም አመልከዋለሁ» በማለት ለፎቶው ተንበርክኮ «ሰግዶ» ከመድረክ ወርዷል።

### ቴዲ ተከተለ

ከአዲሱ ትውልድ አባላት መሀከል ለጥላሁን ምስክርነት ለመስጠት እድል አግኝቶ ከመድረክ የወጣው ድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ) ነው። «የሙያ አባታችን የሆነው ጥላሁን ገሠሠ በተወለደበት ቀን በቅርቡ ከገጠመን የሰው ሀዘን አንፃር ሁሉንም የምናስብበት ነው» ሲል ንግግሩን ያሟሸው ቴዲ «ውጪ ስለ ነበርኩ በቀብር ሥነ-ሥርዓቱ ላይ አልተገኘሁም» በማለት ሳቅ ፈጥሯል። «ጥላሁን በእኛ ጆሮ የሚደመጥ እንጂ የሚነገርለት ስላልሆነ አክብሮቴን ብቻ ብገልፅ ይቀለኛል። ብዙ ያልተነገረለት የሙያ 'ዲሲፕሊኖች' ያሉት ሰው ነው። ከእሱ ልንማር የሚገባን ትልልቅ የሙያ ዲሲፕሊኖች አሉ። ድምፁን ለማሻሻል ሰዓት ይዞ ገንዳ ውስጥ የሚያሳልፍ ሰው ነው። ይህን አሁን ስንቶቻችን እናደርጋለን?» ሲል እኩያ የሙያ ባልደረቦቹን ጠይቋል።

ቴዲ ተመርጠው የተዘጋጁ የሚመስሉ ቃላትን በመወርወር ለጥላሁን ምስክርነቱን መስጠት ቀጥሏል። «ነፍሱ...» አለ ቴዲ «ነፍሱ ንፁህ ነበር። ችሎታ ብቻ ሳይሆን ቀና ልብ ትልቅ እንደሚያደርግ ከእሱ አይተናል። እግዚአብሔርም አክብሮት እንዲሞት አድርጐታል። ይህንን ከእሱ እንደተማርን እርግጠኛ ነኝ» ብሏል።

መስከረም 17 የሙያ አባቱ የጥላሁን የልደት ቀን የሚከበርበት ብቻ ሳይሆን የስጋ አባቱ ካሳሁን ግርማሞን ያጣበትም ቀን መሆኑን በማስታወስ «'በሚች ማዘን የለም' ጭፈራና ሽለላ ነው የሚገባው ጥላሁን አኩርቶናል» ያለው ቴዲ ከጥላሁን ጋር ትንሽ የመቀራረብ እድል አግኝች እንደነበር የገለፀ ሲሆን «የህይወቴ ህይወት»፣ «ከአንድም ሁለት ሦስቴ»፣ «የዘንባባ ማር ነሽ» ከሚሉት የጥላሁን ሦስት ዘፈኖች ላይ ስንኝ በመዋስ በደ/አፍሪካ ህክምና አድርጐ አንድ እግሩን አጥቶ ከተመለሰ በኋላ ጽፎለት የነበረውን ግጥም «ምናልባት ለፕሮግራሙ አስደሳች ሊሆን ይችላል» ብሎ አቅርቧል። የግጥሙ ስንኝ እንዲህ ይሰኛል:-

የህይወቴ ህይወት ነፍሴ ስለሆነ

ለመኖር ሲል ልቤ በእግሬ ላይ ጨከነ፤

ከአንድም ሁለት ሦስቴ ለሞት ያደረሰኝ

ከመሞት ይሻላል ጉሎ ቢያስነክሰኝ፤

የዘንባባ ማር ነው ጣፋጭ ነው መኖር

ይልቅ ላመስግነው ላዳነኝ እግዜር።

ቴዲ ከመድረክ ከመውረዱ በፊት በጥላሁን ገሠሠ የቀብር ሥነ-ሥርዓት ላይ «በስውር ጥበብህ ሳይገባኝ ያከበርከኝ...» ሲሉ የጥላሁን የጥበብ ጓደኞቹና ልጆቹ ያቀነቀኑትን የጋራ ዜማ ለብቻው ተጫውቷል። ይህ ዜማ ቴዲ ከእስር ቤት ከወጣ በኋላ በመድረክ ያቀነቀነው የመጀመሪያ ሥራ ነው። በስፍራው የተገኙ የሙዚቃ ባለሙያዎች የቴዲ ድምጽ ረዥም ጊዜ ያለ ልምምድ አንደመቆየቱ ውበቱ እንዳልተነካና መከርደድም ሆነ መሻከር እንዳልታየበት ለአውራምባ ታይምስ ገልፀዋል።

**በመጨረሻ...**

የጥላሁንን ዝግጅት ለማድመቅ የነፃ አገልግሎት ከሰጠው «ዳዊት ባንድ» ጋር የተለያዩ አርቲስቶች ለማቀንቀን አስቀድመው ፈቃደኝነታቸውን ገለፀው የነበረ ቢሆንም ልምምድ ለመስራት ፈቃኛ የነበሩት ድምጻዊያን ሞገስ ተካና ጌትሽ ማሞ ብቻ እንደነበሩ አንድ የባንዱ አባል ለአውራምባ ታይምስ ገልጿል። ሞገስ ተካ «ድንቅ ሰው» እያለ ለጥላሁን በህይወት እያለ ያቀነቀነለትን ዜማ አቅርቧል። አዲስ አልበሙን ዘንድሮ የለቀቀው ጌትሽ ማሞ ደግሞ የጥላሁንን ዘፈኖች ተጫውቷል። ሞቱን ምክንያት በማድረግ «ሰዎች ምን ይላሉ» የሚል ግጥም በተፈሪ ዓለሙ ቀርቧል። የአምባሰል ሙዚቃ ቤት ባለቤት አቶ ፍቃዱ ዋሬ ለጥላሁን መታሰቢያ የሚሆን የዋንጫ ሽልማት አበርክተዋል። በቀጣዩ ዓመት (በ2010) በሴኔጋል የሚካሄደው 3ኛው የፓን አፍሪካ ፌስቲቫል በጥላሁን ገሠሠ ስም እንዲሰየም ጥረት እየተደረገ መሆኑ ከመድረኩ ተገልጿል።

# የኤርትራ ፕሬዚዳንት አማካሪ፣የማስታወቂያ ሚኒስትሩ እንዲሁም የአገሪቱ የደህንነት ሹም በህገወጥ የመሳሪያ ዝውውር ማዕቀብ እንዲጣልባቸው ኢጋድ በድጋሚ ጠየቀ

ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ በኤርትራ ላይ እርምጃ ሊወስድ ባለመቻሉ ኢጋድ ቅያሜውን በድጋሚ ገልጽዋል። በሶማሊያ የሰላምና የእርቅ አስተባባሪ የሆኑት ኪፕሮቶ ኪርዋ ኤርትራ እና አል-ቃዒዳ በሶማሊያ ውስጥ ታጣቂ ቡድኖችን መደገፋቸውን እና በገንዘብ መደጎማቸውን የሚያረጋግጥ «አሳማኝ ማስረጃ» በኢጋድ እጅ እንደነበር በመግለጽ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ በቃላት ሳይሆን በተግባር አፋጣኝና ተገቢ እርምጃ በክልሉ አዋኪዎች ላይ እንዲወሰድ ጠይቀዋል።

በቅርቡ ኢጋድ እና የአፍሪካ ሕብረት ለአል ሻባብና ለሌሎች አሉታዊ አካላት ድጋፍ በሚሰጡትና በሚደጉሙት በኤርትራና በሌሎች አካላት ላይ ማዕቀብ እንዲጣል ጠንካራ ጥቆማ ማድረጋቸው ይታወሳል። የተባበሩት መንግስታት የጸትታው ምክር ቤት ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ አሜሪካም ግፊት ማድረጓ ይታወቃል። ሆኖም የምክር ቤቱ ሌሎች አባላት - ቻይና፣ ፈራንሳይ፣ ሩሲያ እና ዩናይትድ ኪንግዶም - በሪዞሉሽኖቹ ላይ ልዩነት ፈጥረዋል።

ሪዞሉሽኖቹ የጦር መሣርያ እና የውጭ ተዋጊዎች ወደ ሶማሊያ እንዳይገቡ ለመከላከል በክልሉ የአየር እን የባህር ትራንስፖርት ገደብ እንዲጣል የማድረግን ሀሳብ ያዘሉ ነበሩ። ከዚህ በተጨማሪ በሶማሊያ ቀውስ ላይ የተሳተፉ ግለሰቦችን ንብረቶች እንዳይንቀሳቀሱ እና ግለሰቦቹም ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስ ገደብ እንዲጣልባቸው የሚያደርግ ሀሳብ በሪዞሉሽኖቹ ተካቷል።

በሶማሊያ ቀውስ ከተሳተፉ ግለሰቦች ዝርዝር ውስጥ የኤርትራ መንግስት ከፍተኛ ባለስልጣናት ተጠቅሰዋል። በሶማሊያ ቀውስ በመሣርያ ዝውውር እንቅስቃሴ ላይ ተሳትፈዋል ከተባሉት መካከል የኤርትራ መንግስት የፖለቲካ ጉዳዮች ኃላፊና በህዝባዊ ግንባር ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ የፕሬዝዳንቱ አማካሪ የሆኑት አቶ የማነ ገብርዓብ፣ የኢንፎሜሽን ሚኒስትሩ አቶ አሊ አብዱ፣ እና የደህንነት ሹሙ ጠዓመ አብረኻሥላሴ ይገኙበታል።

## መጣጥፎች

# ደመራ ተኮር ወሬዎች

## አዲስ አበባ ቁጭ ብለን «የእኛ ሰው በአሜሪካ» ከተባልን ሰዎች...

አቤ ቶኪቻው

abeto2007@yaoo.com

**እንኳን ለብርሃነ መስቀሉ በሰላም አደረሰዎ!**

መግቢያ፡- ባሳለፍነው ሳምንት ውስጥ በከተማችን ከሚታተሙ ጋዜጦች በአንዱ ላይ አንድ ፅሁፍ ያነበቡ ወዳጆቼ ስልክ መቱልኝ፡፡ የስልኬን አረንጓዴ ተጭኜ ትህትና በተሞላበት ድምፅ አቤት አልኩኝ፡፡ ከወድያኛው መስመር ያለው ሰው ድምፄን የተጠራጠረ ይመስል «ኢትዮጵያ ውስጥ አለህ እንዴ?» ቢለኝ «አለሁኝ ወዳጄ!» አልኩት በተጨማሪ ትህትና! «በአንድ ጋዜጣ ላይ «ከአሜሪካ አቤ ቶኪቻው የላከው ደብዳቤ» ተብሎ አይቼ ደህና ሰው አይበረክትም ይሔ ሃገር ወዳድ ሰው እንዴት ሳይሰናበተን አሜሪካ ገባ ብዬ ነው የደወልኩልህ፡፡» ቢለኝ ጠላትዎ ክው ይበል ክው አልኩኝና ያለሁበትን አካባቢ ማጣራት፡፡ ፊት ለፊቴ «የእናት ጓዳ ምግብ ቤት»፣ ዘወር ስል «ላሳምረው ጋሼ?» የሚል ሊስትሮ፣ አሁንም ዘወር ስል «ሳንቲም ልስጥህ?» የምትል ሚጢጢ ህፃን፣ እንደገና ዘወር ስል «የዕለት ጉርሴን ስጡኝ» የሚሉ አዛውንት፣ ደግሜ ዘወር ብል «ፒያሳ አራት ኪሎ የሞላ» እያለ የሚጠራ ያልሞላ ሰማያዊ እና ነጭ የተቀባ ታክሲ... ይሄንን ሁሉ ካስተዋልኩኝ በኋላ «ኧረ ጌታዬ አዲሳባ ውስጥ ነኝ የምን አሜሪካ!?» ብዬ መመለስ! ታድያልዎ ወዳጄ ተገርሞ ተገርሞ «ምን አይነት ዘንድሮ መጣ! ሲል እያማረረ አዲሳባ እያለህ የእኛ ሰው በአሜሪካ ስትባል አይገርምህም?» ብሎ መጠየቅ፡፡ እኔም መልስ አጥቼ ዝም፡፡ ነገሩ ሲብራራ፡- በአንድ የከተማችን አንጋፋ ጋዜጣ ላይ ከዚህ በፊት በአውራምባ ታይምስ መፅሔት ላይ ወጥቶ የነበረ «የካድሬው የፍቅር ደብዳቤ» የሚል የእኔ ፅሁፍ ከአሜሪካ የተላከ ተብሎ ወጣ፡፡ ወዳጆቼም ቅር ተሰኙ፡፡

ለነገሩ ፀሀፊው እግዜር ያክብረው (ይቅርታ «ያክብራቸው» እርጅና የተጫናቸው ሰው ባይሆኑ አዲሳባ ቁጭ ያለውን ሰው የእኛ ሰው በአሜሪካ አይሉም ተብሎ ስለሚጠረጠር ፀሀፊውን አንቱ ለማለት እወዳለሁኝ) እናም እግዜር ያክብራቸው እና እኔ እዚህ አዲስ አበባ ከሃገሬ ከጥጋቧ ከፀሀዩ መንግስቴ ፍቅር ይዞኝ ቁጭ ባልኩበት ከአሜሪካ ደብዳቤ ላከልኝ ያሉት ትህትና ይዟቸው እንጂ «ሟች ከመሞቱ በፊት የፃፈልኝ ደብዳቤ» ብለው ሊያቀርቡ ይችሉ አልነበረምን? እናም እደግመዋለሁኝ እግዜር ያክብራቸው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ትዝ ያለኝን እና ከመግቢያው የተረፈውን ከወደ መዝጊያው አካባቢ አወጋዎታለሁኝ፡፡

እንደምን ሰነበቱ ወዳጄ? በዓሎቹ እንደምን ይዘዎታል? አውድ አመት በአውድ አመት ላይ እየተደራረበ ከተማችንን ሞቅ ሞቅ አደረጋት አይደለም እንዴ? ደመራው እንዴት ነበር? አወዳደቁ ጥጋብ ወደሚያመጣ አቅጣጫ ነው ተብሏል፡፡ ጎሽ!

ወደ መስቀል አደባባይ ከሄድኩባቸው አመታት በሙሉ እንደ ዘንድሮ ስርአት ያለው የሰከነ የመስቀል አከባበር አላየሁኝም፡፡ እንዴ ብፁዕ አባታችን ራሳቸው እኮ ከንግግር ማድረጊያው

እስከ ደመራው በእግራቸው ነው የሄዱት:: አምና በመኪና ነበር ከዚህ ምን እንረዳለን? ብዬ አንድ ወዳጄን ብጠይቀው «ዘንድሮ ከፍተኛ የነዳጅ ጭማሪ መኖሩን» አለኝ:: ይህ በልቡ ክፋት ያደረ ወዳጄን ልቦና ይስጥህ እያልኩት እኔ ግን እላለሁኝ:: ይህ የሆነው የተረጋጋ ክብረ በዓል በመሆኑ ነው:: ለዚህም ከዋዜማው ጀምሮ በአዲስ ልብስ ሽክ ያሉት ፖሊሶቻችን «ገለታ» ይግባቸው ማለት ይገባል:: (እነርሱም እኮ ህዝቡ ምስጋና ይገባዋል ብለዋል:: እንዲህ መመሰጋገኑ ይሻላል አይደል እንዴ ፖሊስ ነብሴ!?)

ኧረ ቆይ ወዳጄ ደመራው ላይ የሆነውን ልንገርዎት:: ብፁዕ አባታችን ሆዬ የመግቢያ ንግግር በአማርኛ ተናግረው ካበቁ በኋላ ለውጪ ሃገር እንግዶቻችን በእንግሊዝኛ ልናገር ብለው ምዕመናኑን ፈቃድ ጠየቁልዎ... ምዕመናኑም «መቼስ ካሉ ምን ይደረግ!?» ብሎ ዝም አለ:: ከዚያም ከአንድ ዲፕሎማት የሚስተካከል እንግሊዘኛ አፈሰሱልዎ... (አይ መማር ደጉ!) ይሔን ጊዜ አንዱ ወዳጃችን «ይቅር ይበለኝና...» ሲል መናገር ጀመረ:: እኛም «ይቅር ይበለንና» መስማት ጀመርን:: «አባታችን አማርኛ ሲናገሩ ሽማግሌ እንግሊዝኛ ሲናገሩ ጎረምሳ ይመስሉኛል::» አለን:: «ይቅር ይበለንና» ሳቃችን መጣ:: ሳቅን:: የሆነ ሰዓት ላይ ደግሞ አንድ እንግሊዘኛ በተናገሩ ጊዜ በአንድ አካባቢ የተሰበሰቡ ሰዎች ጭብጨባቸውን ቢያቀልጡት ጊዜ አንዱ ለእንግሊዝኛ ባዳ የሆነ ወዳጃችን «ምን ተናግረው ነው የተጨበጨበው?» ብሎ ሲጠይቅ እኛ በትህትና ልንመልስለት ስንል «ይቅር ይበለውና» አንዱ «የሚያጨበጭቡት ከየትምህርት ቤቱ የተወከሉ እንግሊዝኛ መምህሮች ናቸው በአባታችን እንግሊዝኛ ተደስተው ነው» አለው:: እኛም እንዲህ የተናገረውን «ይቅር ይበልህ» ብለን ቁልፍ ወይም ዚፕ ብቻ ትንሽ ብረት ነክ ነገር በአፉ ያዝ እንዲያደርግ መከርነው::

ከዚህ ከደመራ ጋር በተያያዘ አንድ ጨዋታ እንጨምር:: በየደብሩ መስቀል አደባባይ ሔዶ ችቦ ማብራት የሚፈልጉ ሰዎች እንዲመዘገቡ ጥሪ ተላልፎ ነበር አሉ:: (ልብ አድርጉ አሉ ብያለሁኝ ጨዋታዋ እኔ ጋ የደረሰችው በስሚ ስሚ ነው) ይህንን የአሉ ወሬ ይዘው «ምናባዊ» ወዳጆቼ እንደሚከተለው ተነተኑት::

<u>ዛሬ</u>፡- «ችቦ ማብራት የምትፈልጉ ሰዎች እየመጣችሁ ተመዝገቡ» ተባለ ተመዘገቡ:: ችቦም አበሩ ደስታም ሆነ::

<u>ወደፊት</u>፡- ደመራው ሊበራ አስር ወር ሲቀረው በሬድዮ ማስታወቂያ ይነገራል:: «እንዳያመልጥዎ የደመራ ችቦ ለማብራት ዛሬውኑ ይመዝገቡ በእድልዎ ይጠቀሙ» የሚል ይዘት ያለው ማስታወቂያ በሬድዮ እና በቴሌቪዥን ይተላለፋል:: ከዛም በአሉ ሊደርስ አንድ አስር ቀን ሲቀረው በአዲስ ልሳን ጋዜጣ የደመራ ማብራት እድለኞችን ዝርዝር የያዘ ጋዜጣ ይወጣና «ስምዎን ይመልከቱ ሃምሳ ሃምሳ ብር» ይባላል:: (ምናበኛ ወዳጆቼ ይህ በዕውነት ሟርት ነው)

ወደ በዓሉ ስንመለስ፡- አመትባልን አመት በዓል የሚያስመስሉት ሬዲዮኖቻችን እና ቴሌቪዥናችን ጥጋባዊ እና ባህላዊ ዘፈን እያስዘፈኑ ርሃባችንን አስረሱን እኮ! (የቱን ርሃብ? አሉኝ እንዴ ወዳጄ ምናባቴ አውቃለሁኝ በጥጋብ ሃገር ላይ ቁጭ ብዬ ስለ ርሃብ ሳወራ በመገኘቴ በእውነት ፀፀት ተሰምቶኛል፡፡ እናም ሂሴን ውጫለሁኝ፡፡ ሌላ የሚዋጥ ነገር እንኳ ቢጠፉ «የእኛ ሰው በአዲስ አበባ» ሂስ እየዋጠ ይቺን ክፉ ጊዜ ማለፍ አቅቶት ስለ ርሃብ አወራ ቢባል ነውር አይደለም እንዴ? ደግሞ የምን ክፉ ቀን አመጣሁኝ? የእኔ ነገር ዞሮ ዞሮ እዛው ሆነና አረፈው አይደለም? ግዴልዎትም ወዳጄ ዛሬ ነገር ነገር ያለኝ አስመሰልኩት እኮ ከአሁኑ ሰላም ያሰንብትህ ይበሉኝ እስቲ)

ቀጥሎ ስለ ጥጋብ አወራለሁኝ፡፡

አመትባሉ ሞቅ ደመቅ ብሏል፡፡ የሀገሬ ሰው በነጭ የሀገር በዓል ልብስ አሸብርቆ ነጭ ጭራውን እያወዛወዘ መርቆ፣ ነጭ በሬ አርዶ፣ ነጭ ጮማ እየቆረጠ ነው፡፡ ለማወራረጃ ንፁህ የማር ጠጅ አለ፡፡ (እሰይ እንዲህ ነውንጂ አመት በአል!)

ቀዩ ስጋ ድቅቅ ብሎ ተከትፏል፡፡ የቀለጠ ቅቤ እንደ ውሃ በላዩ ላይ ተደፋበት፡፡ ባለሞያዋ ወይዘሮ በአንዳች ማለቆጫ ስጋውን እና ቅቤውን አዋሃደችው ወድያው በቅቤ ሳብያ የሚጠጣ በስጋ ሳቢያ ደግሞ የሚበላ የመሰለ ክትፎ እያቃጠለ ከሚጣፍጥ ሚጥሚጣ ጋር ቀረበ፡፡ (በሞቴ ይብሉልኝ አፈር ስሆን አንድ ጉርሻ ግብዣው ቀለጠ!)

ቀኑ አመትባል ነው፡፡ እናም ሁሉም ቤት ይህ አለ፡፡ ፈንዲሻው፣ ዳቦው፣ ቆሎው፣ ቡናው፣ ፀአዳ ልብስ፣ የሚያማምሩ ህፃናት፣ ጭፈራ፣ ድለቃ ይህ ሁሉም ቤት ይገኛል፡፡ ምክንያቱም አመት በዓል ነው፡፡ ታድያ ሰው እንዴት በአመት በዓል ምድር ባዶ ቤት ይውላል? ወዳጄ ይህ አለም ከወዴት አለ? ብለው አይጨነቁ ኢቲቪ ለዘላለም ይኑር ለክሊፖቻችን ረዥም ዕድሜ ይስጥልን፡፡ ጮማ ምን ነበር? የጠጅ መልክ ምን አይነት ነው? ክትፎ እንዴት ነበር የሚሰራው? ብሎ ለሚጠይቁ በአሉንም እንደምን እናሳልፍ ብለው ለተጨነቁ አልኳቸው፡፡ የኢቲቪ ልዩ ዝግጅት እና የባህል ዘፈኖቻችንን ተመልከቱ ከእኛ ዘንድ የሌለው ጥጋብ እነርሱ ዘንድ አለ፣ ከእኛ የራቀው ፍስሃ በዛ ይገኛል፣ እነሆ የድሎት ቤቱ የት ነው ክሊፖች እና የኢቲቪ ልዩ ዝግጅት ውስጥ አይደለምን? ደሃ ድህነቱን ይረሳ ዘንድ ክሊፕ ይክፈት የቴሌቪዥን ልዩ ዝግጅትም ይመልከት፡፡ ይህ ነው የዘንድሮ ጥጋብ! (ተመስገን ይህንን አታሳጣን በሉ!)

እኔ የምልዎ ወዳጄ.... ከላይ ስለ «የእኛ ሰው በአሜሪካ» ስናነሳ ትዝ ያለኝ አለ ብዬዎትም አልነበር? ሰሞኑን የእኛ ሰዎች ወደ አሜሪካ ተጉዘው ነበር፡፡ ያው መቼም ለሰዎቻችን የሚሆን ስብሰባ አይጠፋምና ከማይጠፉት ስብሰባዎች በአንዱ ለመካፈል ነበር ጉዞው፡፡ እስከዛሬ ብቻቸውን ወይም ከሌሎች ባለስልጣኖች ጋር ይሔዱ የነበሩት ጠቅላይ

ሚኒስተራችን ዛሬ ከቀዳማዊት እመቤታችን ጋር ነበር የሔዱት፡፡ እኛ እዚህ ያለን ከራሳችን ኑሮ ይልቅ ለእርሳቸው ረዥም ዕድሜ በመመኘት ዕድሜያችን የገፋ ሰዎች ሰላም ያመጣቸው ዘንድ እየፀለይን ሳለ ታድያ በየ ኢንተርኔቱ ሃሜቱ ቀልጥልዎታል፡፡ የምን ሃሜታ አሉኝ እንዴ? ኧረ ነገሩስ ለወግም አይመች... ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን እና ባለቤታቸው ቀዳማዊት እመቤት መኪና ውስጥ ትንሽ አለመግባባት ብጤ.... ለነገሩ የኢንተርኔት ነገር አይታመንም፡፡ ብቻ ጭቅጭቅ ነገር በአሜሪካው ፕሬዚዳንት እና ባለቤታቸው ፊት አሳዩ ብለው እየዘገቡ ነው፡፡

ይህንን የሰሙ አንዳንድ ትንሽ ነገር የሚበቃቸው ነገር አጋናኞች ከተቃዋሚ ፓርቲ ጋር ተስማምተው እና ተቻችለው መጪውን ምርጫ «እንከን የለሽ» ያደርጉታል ስንል ምነው ጌታችን እና እመቤታችን መቻቻል አቃታቸው? ሲሉ ቧልተዋል፡፡ እኛም «የእኛ ሰው በአሜሪካ አደረገ የተባለው ሁሉ እውነት አይምሰላችሁ!» ስንል ማስተባበያ ስንሰጥ ሰንብተናል፡፡

*<u>በመጨረሻም</u>*

ጨዋታችን አመት ባል አመት ባል ብሎ ያበቃ ዘንድ በዛሬው መጨረሻችን ላይ በቲቪ ስንመለከት ከነበረው የአመት ባል  ልዩ ዝግጅቶች ስለ አንዱ እንደሚከተለው እናውጋ፡-

ግብር የምንከፍልበት ቴሌቪዥን ጣቢያችን ለአመት በአላችን ልዩ ዝግጅት ማዘጋጀት አቅቶት (ግብሩን ሳናሳንሰው አልቀረንም መሰል) የልማታዊ ባለሃብቶችን የብርኢዩቤልዩ ምስረታ በዓል  እናከብር ዘንድ አስገድደውናል፡፡ በዝግጅቱ ላይ ባለ ሃብቱ ከልጆቻቸው ስጦታ ሲቀበሉ ሰራተኞቻቸው ሲሞሽሩ ትጉህ ሰራተኞቻችንን ሲሸልሙ፣ከአሜሪካ ልጆቻቸው የላኩት ደብዳቤ ሲያነቡ ወዘተ... ተመልክተናል፡፡ ኢቲቪም ሌሎች ባለሃብቶች የእኒህን ባለሃብት አርአያነት እንዲከተሉ አደራ የሚል መልዕክት አስተላልፏል፡፡ ጎሽ! አሁን አፈር ስሆን  «ምን ናፈቀህ?» ይበሉኝ፡፡ ልማታዊ ባለሃብት መሆን «ከዛስ» አይሉኝም? ከሰኞ እስከ አርብ ያለውን የአየር ሰዓት መግዛት፡፡ ከዛ «የመስቀል በዓል ልዩ ስፖንሰር» ተብዬ የራሴን በዓል ብቻ ማክበር! ምን እሱ ብቻ ገንዘብ ጨመር ካደረኩኝ ዜና የለ ህዳሴ ማብሰር የለ ከጠዋት ቁርስ አበላሌ እስከ ምሽት አልባሌ ሁሉንም በቀጥታ እንዲተላለፍ ማድረግ፡፡

ኢቲቪዎች አደራ እኔ ሃብታም ስሆን «ባለ ሃብቶች ያየር ሰዓት ግዙን» ማለታችሁን እንዳትረሱት፡፡

ወዳጄ እንዲህ እንዲህ እያልን የመለያያችን መስመር ላይ ደርሰናል፡፡ ስናውቅ በድፍረት ሳናውቅ በስህተት የተናገርነውን በሰማይ መሃሪ አባታችን በምድርም ፀሀዩ መንግስታችን ይቅር ይበለን! እባክዎ ወዳጄ ጮክ ብለው አሜን ይበሉ!

አማን ያሰንብተን!

# ርዕዮተ-ዓለም ወይስ ድርጅታዊ የብቃት ማነስ?

**በጃዋር ሲራጅ መሀመድ**

በቅርቡ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) ያለፉ ሁለት አስርት ዓመታትን ከዳሰስኩባቸው ጽሁፎቼ ለአንደኛው ፕ/ር መሳይ ከበደ በሰጡት ምላሽ፣ ለኦነግ ውድቀት ቀዳሚ ምክንያት የሆነውን ሳልዳስስ ማለፌን ሞግቷል፡፡ እንደእርሱ እምነት፣ ለኦነግ ስኬት ዋናው እንቅፋት የድርጅቱ ርዕዮተ-ዓለም ነው፤ ማለትም፣ የራስን እድል በራስ መወሰን ከሚለው አቋሙ ውልፍት አለማለቱ ነው፡፡ በዚህ ከፕ/ር መሳይ ከበደ ጋር አልስማማም፡፡

እንደማስበው፣ የርዕዮተ-ዓለም «ትክክለኛነት ማጣት» ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ኦነግ የኦሮሞን ጥያቄ ለማራመድ እንዳይችል አድርጎታል በሚለው መከራከሪያ ፕ/ር መሳይ ተሳስቷል፡፡ ይህ ሙግቱ ተቀባይነት ሊኖረው ይችል የነበረው በግንባሩ የተቀነቀነው ርዕዮተ-ዓለም፣ ድርጅቱ እየተሟገትኩለት ነው የሚለውን ሕዝብ መሳብ የተሳነው ወይም በሕዝቡ ወድቅ የተደረገ ቢሆን ኖሮ ነበር፡፡ መከራከሪያዎቼ፣ ኦነግ ያልተሳካለት ከኦሮሞ ብሔር ድጋፍ በማጣቱ ነው ብለን እንድናምን የሚመሩን ናቸው፡፡ ለክፍለ ዘመን በባሕላዊ፣ በፖለቲካዊና በኢኮኖሚያዊ አድሎ፣ በሰብዓዊ ክብር ውርደትና በጭቆና የተሰቃየ ሕዝብ እንደመሆኑ፣ እልፍ አእላፍ ኦሮሞ በተፈራራቂ አገዛዞች ተሸክሞት ከነበረው የጭቆና ሥርዓት ለመላቀቅ የራስን እድል በራስ የመወሰን ጥያቄን እንደመንገድ ተቀብሏል እንዲሁም በስፋት ደግፎአል፡፡

መሪዎች በዚህ የተለየ ርዕዮተ-ዓለም ዙሪያ ሕዝቡን ማሰባሰባቸው ትክክል ነበር ወይስ አልነበረም የሚለው ሌላ ጭብጥ ነው፤ ሆኖም፣ ድርጅቱ ለአራት አስርት ዓመታት ያህል አስደናቂ ድጋፍ እንዳያገኝ ርዕዩተ-ዓለሙ ያገደው ባለመሆኑ ያ ጥቅም የለውም፡፡ ያ ነው ርዕዩተ-ዓለምን ለኦነግ ውድቀት ተጠያቂ ያላደረኩበትና ከዚያ ይልቅ ድርጅቱ ስለምን ያን መሰል ሕዘባዊ ድጋፍ መጠቀም አልተቻለውም ወደሚለው ማብራሪያ ትኩረቴን ያደረኩበት ትክክለኛው ምክንያት፡፡ በተሳሳቱ የስትራቴጂ ምርጫዎችና በውስጥ የፓርቲ ሽኩቻዎች ምክንያት ተጨባጭ ውጤቶችን ማምጣት አለመቻል ድርጅቱ ራሱን ወደከተተበት ቀውስ መርቶታል ብዬ ወደሚል ድምዳሜ ደርሻለሁ፡፡

በተጨማሪ፣ አንድን ሽማቂ ይረዳሉ ተብለው የሚታመኑ ሁሉም ወሳኝ ሁኔታዎች ኦነግ እንደነበረው ማጤን አስፈላጊ ነው:: እነዚህ የሚያካትቱት፣ ዝቅተኛ «ጂዲፒ» ለእያንዳንዱ ሰው መድረስ (ለደካማ መንግስት ለእጅ አዙር)፣ አስቸጋሪ መልከዓ-ምድር (ከመሀልና ከገጠር ርቀት፣ ጥቅጥቅ ደን)፣ እና በመሀል ሀገር የተቆጣ አያሌ ሕዝብ::

### የሽማቂ ብቃት:- የስትራቴጂ ምርጫና የአመራር ቆራጥነት ወይስ ርዕዮተ-ዓለም?

የአንድ ሽማቂ ርዕዮተ-ዓለምና ተቀዳሚ ፕሮግራም በማዕከላዊ የድጋፍ መሰረቱ ተቀባይነት እስካገኘ ድረስ፣ አብዛኛው ተከታዩ ስኬት የሚወሰነው በስትራቴጂና በአመራር ቆራጥነት ላይ ነው:: የፕ/ር መሳይን መከራከሪያ የተከተልን እንደሆነ የኮሎኔል መንግስቱን አገዛዝ ለመገርሰስ ህወሓትንና ሻዕብያን የረዳቸው ያራመዱት ርዕዮተ-ዓለም ነው በማለት መደምደማችን አይቀርም:: በመሆኑም፣ ሕወሓት ማዕከላዊ ሥልጣን ለመያዝ የቻለው ርዕዮተ-ዓለሙ በኢትዮጵያ ሕዝብ መጠነ ሰፊ አብላጫ ተቀባይነት በማግኘቱ ነበር ብለን ማመን አለብን:: ጉዳዩ እንደዛ እንዳልነበር የምናውቀው ነው:: ሕወሓት በመነሻ ምዕራፉ ማድረግ የነበረበት የትግራይን ህዝብ ከጭቆና ቀንበር የማውጣት ፕሮግራሙን ማስተዋወቅ ብቻ ነበር:: በማዕከላዊው መንግስት ላይ በነበረው መጠነ ሰፊ ቁጣ፣ ገበሬው ከርዕዮተ-ዓለማዊ ክርክር ይልቅ ስቃዩ የሚቋጭበት በይበልጥ ያሳሰበው ነበር::

በይበልጥ ቆራጥ አመራር፣ ድርጅታዊ ዲሲፕሊንና ብልጣብልጥ ስትራቴጂና ፓለቲካዊ ቅስቀሳ፣ ግንባሩ ፈጣን ወታደራዊ ስኬት እንዲቀዳጅና የመንግስት ሥልጣን የመጨበጥ ግቡን ለማሳካት ያስቻለውን የሕዝብ ድጋፍ ለማስጠበቅ ረድቶታል::

እርግጥ ነው እዚህ ጋር የሕወሓት አመራር በአመራር አካሄዱና በማደራጀት መርሁ ላይ ጠርዝ የደረሰ ስታሊኒስታዊ አስተሳሰብ፣ ማለትም የአልባኒያውን ኤንቨር ሆክሳን ዓይነት፣ ከመቅዳት አልተመለሰም፤ በመሆኑም፣ ስኬትን ለመቀዳጀትና ላለፉት 18 ዓመታትም ሥልጣን እንደያዘ ለመቀጠል ችሏል:: እናም ኦነግ ትግሉን ወደስኬት ለመምራት የአለመቻሉ እውነታ በስታሊኒዝም ሊመካኝ አይችልም ብሎም መከራከር ይቻላል:: ከኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ዩኒየን (ኢዴዩ) ቀጥሎ በይበልጥ ኦነግ፣ መሰረታቸውን ከበርካታ የ«ኢትዮጵያ» ብሔርና «ክፍል» ላይ ከመሰረቱ ድርጅቶች የመጨረሻው ግራ-ዘመም የፖለቲካ አመለካከት አራማጅ ድርጅት ነበረ ማለት ነው ብሎም መከራከር ይቻላል:: ኦነግ ካለው የብሔርተኝነት አጀንዳው በስተቀር፣ በግራ-ዘመም ርዕዮተ-ዓለማዊ ዝንባሌው አይታወቅም::

የአንድን ሽማቂ ውድቀትና ስኬት ለመወሰን ርዕዮተ-ዓለም እምብዛም አስተዋጽኦ እንዴት እንደሌለው ለማስረጽ እስኪ አንድ ተጨማሪ ምሳሌ ላንሳ፤ ፕሮፌሰሩ ከጠቀሷቸው

ድርጅቶች ጋር በአንድነት ለመጠቀስ በሚገርም መልኩ የዘነጉትንና ከጽንፈኛ ግራ-ዘመም ንቅናቄዎች የፈለቀውን ኢሕአፓን ከተመለከትን፣ ያስቀመጠውን ግብ ከማሳካት ያደናቀፈው ቀዳሚው ምክንያት የተከተለው ርዕዮተ-ዓለም ነው ብዬ አላምንም፡፡ የኢሕአፓ ፓለቲካዊ አጀንዳ ከዋና የድጋፍ መሰረቶቹ - ከቢሮክራት ምሁሮችና ከአማራ ሕዝብ - አዎንታዊ ተቀባይነትና ድጋፍ ነበረው፡፡ እርግጥ፣ በወረቀት ደረጃ በወቅቱ ከነበሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች አንፃር ኢሕአፓ በይበልጥ ሁሉን አሳታፊ ፕሮግራም ነበረው ብሎ መከራከር ይቻላል፡፡

ለእኔ የኢሕአፓ መውደቅ ቀዳሚው ምክንያት የሚመነጨው የፓርቲውን በጣም ብቁ አመራሮች፣ ስትራቴጂስቶችና የከተማ መዋቀር ያንኮታኮተው፣ ወታደራዊው መንግስት ሕዝባዊ ድጋፍ እያለው ሳለ፣ በተለይ እንጭጭ የሽምቅ ጦርነት ለማወጅ ከተወሰነው ውሳኔ ነው፡፡

የከተማው መዋቅር መበታተን በአመራሩ ውስጥ ንዴት፣ የአቅጣጫ መሳትና የሞራል መንኮታኮት ያስከተለ ትልቅ ሽንፈት ነበር፤ አክራሪ ግራ-ዘመም ድርጅት እንደመሆኑ፣ አመራሮቹ የጋራ ሽንፈታቸውን ከመቀበል ይልቅ ወደ መወነጃጀል ገቡ፣ የተለየ አመለካከቶች ያላቸውን ቀጡ፡፡

የውስጥ ሽኩቻው ዳግም ለመደራጀትና ለመመለስ ታላቅ እንቅፋት እንደነበር ግልጽ ነው፡፡ ይህ ፓርቲው የገበሬውን ድጋፍ ለማግኘትና የግዛት ቁጥጥሩን ከሕውሓት ለማስበለጥ መፎካከር የነበረበት ከመሆኑ እውነታ ጋር ተደምሮ ድርጅቱ ምንም ዓይነት ተጨባጭ ውጤቶች እንዳያስመዘግብ በጣም አስቸጋሪ እንቅፋት ነበር፡፡ የመጨረሻው ሞት በአመራሩ ትግሉ ከነአካቴው መተዉ የነበር ሲሆን ያም ምንም ዓይነት እድልን የሞተ ያለቀለት አደረገው፡፡ በመሆኑም፣ ልክ እንደ ኦነግ፣ ከኢሕአፓ መፈረካከስ በስተጀርባ ያለው ዋናው ጉዳይ ተጨባጭ ውጤት ለማምጣት አለመቻል ነው፡፡ ያም ውድቀት የተሳሳተ ስትራቴጂ ውሳኔና የውስጣዊ ሽኩቻ ውጤት ነው፡፡

በተጨማሪ፣ ኢሕአፓ ግራ-ዘመም አጀንዳውን እስከ 1980 ድረስ አሻሽሎት ነበር፤ እናም በልዑል ራስ መንገሻ ስዩም የተመራ ፓርቲ አቋቋመ - የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ዩኒየንን (ኢዴዩ)፡፡ ግና ጥምረቱ ባለፉት 29 ዓመታት ለፓርቲው ምንም ነገር አላመጣም፡፡ በመሆኑም የኢሕአፓ ተሞክሮ እንደሚመሰክረው፣ የአንድን ድርጅት ርዕዮተ-ዓለም መለወጥ ስኬትን አይቀዳጅም፡፡

**ለውጥ የሞራልና የፖለቲካ ካፒታል ይጠይቃል**

የአንድ ሸማቂን የውጪ ግንኙነቶች ርዕዮተ-ዓለም ተጽዕኖ ማሳደሩ የሚቀር አይደለም፡፡ ኦነግ የራስን እድል በራስ የመወሰን ግቡን ተግባራዊ ለማድረግ መንቀሳቀሱ ተቃዋሚዎች ንቅናቄውን ገነጣጣይ ብለው ለመፈረጅና በሌሎች ኢትዮጵያውያንና በተወሰኑ

ዓለም አቀፍ አካላት ዘንድ ፍራቻና ተቃውሞ ማስነሳቱ በተጨማሪ ግልጽ ነው። ሆኖም ኦነግ የራሱን የድጋፍና የኃይል ማዕከላዊ መሰረት በብቃት በመጠቀም ራሱን ሕይወት ያለው ኃይል ለማድረግ ባለመቻሉ፣ የውጭ አጋርነት ያስፈለገበት ደረጃ ላይ ጭራሽ አልደረሰም። ሽማቂ አንዴ ጠንካራ ከሆነና ብቃቱን ለድጋፍ መሰረቱ ካረጋገጠ፣ አመራሩ ጠቅላላ ፕሮግራሙን በማሻሻልና ዳግም በመቅረጽ፣ ለዚህም የውጭ ድጋፍ ለመሳብ የሚያስችለውን በቂ የሞራልና ፖለቲካዊ ካፒታል ያገኛል። ሆኖም በብቃት ማጣትና በውስጥ ሽኩቻ ብቃቱ የመነመነ ድርጅት የፈለገ አስፈላጊነቱ ቢታየው እንኳ ርዕዮተ-ዓለሙን መለወጥም ሆነ ማሻሻል የሚቻለው አይደለም።

ባለፈው አስር ዓመት የኦነግ አመራር ሉዓላዊት አገር የመመስረት ግቡን ለመተው ዙሪያ ገባውን ሲሽከረከር መቆየቱ የተደበቀ አይደለም፣ ሆኖም ግን እንደዛ ለማድረግ አልተቻለውም። አመራሩ «የተነሳበት» ግብ ጠንካራ ድጋፍ አለው የሚለውን እምነት ለማጠናከር የሚያስችለው የፖለቲካ ካፒታል የለውም እናም ተቀናቃኞቻቸው ለውጥ አቀንቃኞቹን በራዥች በማለት ያስወግዱናል የሚል ፍራቻ አለባቸው። በተቃራኒ፣ ውጤታማ አመራር የለውጥ ተቃዋሚዎችን ዝም ለማሰኘት የሚያስችለው የሞራል ካፒታል ሊኖረው ይገባ ነበር። የሕወሓት ወታደራዊ ስኬት ትግራይን ነፃ የማውጣት አጀንዳውን ለመከለስ ያቻለውን በቂ ጊዜ የሰጠው ሲሆን ይህም ወደትልቁ ጉዞ ማለትም ጠቅላላዋን ኢትዮጵያ ወደመያዝ መርቶታል። ምንም እንኳን ክለሳው በድርጅቱ ውስጥ ተቃውሞ ያስከተለ መሆኑ ግልፅ ቢሆንም፣ አውጋዦቹ አልተሳካላቸውምና ለውጥ አቀንቃኞቹ አልከሰሩም ነበር። ምክንያቱም ደጋፊዎቻቸው በስራቸውና በባለፉት ዓመታት ስኬቶቻቸው ረክተዋልናም።

**ሰላማዊ ትግል?**

ፕ/ር መሳይ ያነሳው ሌላው ነጥብ፣ ኦነግ «ሰላማዊ» ትግል መምረጥ ነበረበት የሚለው ነው። ይህ በጣም የሚያደናግር ነው። ሰላም የግጭት አለመኖር ወይም ግጭትን በተግባር መከላከል ማለት በመሆኑ ምክንያት በአምባገነንነት ላይ የታወጀ የትኛውም የትግል ዓይነት «ሰላማዊ» ሊሆን አይችልም። ግና ፕ/ር መሳይ እንደተቃዋሚ አንድን አምባገነን ሁሉንም ጥቅሞቹንና ሥልጣኑን እንዲተዉና በፊት በፈፀሚቸው ወንጀሎች ተጠያቂ ለማድረግ እየጠየቀ ነው። ይህ ደግሞ ካለፍልሚያ ሊሆን የሚችል አይደለም።

ፕ/ር መሳይ ስለአመጽ-አልባ ትግል እያወራ ከሆነ፣ ፍጹም ከ«ሰላማዊ» ጋር የተቃረነ ነው። ራሱ አመጽ-አልባ ትግል ግጭት ነው፤ ምክንያቱም፣ በተጨባጭ ፍልሚያና መስዋዕትነተት የተሞላ ትግል ነው። አመጽ-አልባ ትግል አምባ-ገነንን የመዋጋት የምርጫ ዘዴ ነው። እናም፣ ተሟጋቾች ለማራመድ በሚፈልጉት አይነት ርዕዮተ-ዓለም የግጁታ ይወስናል ማለት አይደለም። የተመረጠው በሃይማኖታዊ ወይም በ«ሰላማዊ» እምነት

ምክንያት አይደለም፤ ሆኖም፣ ከትጥቅ ትግል የተሻለ ስትራቴጂካዊ እና ታክቲካል ብልጫ ያለው በመሆኑ ምክንያት ነው። ለተመሳሳይ ግብ - ለምሳሌ፣ ዴሞክራሲን ወይም ሉዓላዊት አገር ለመመስረት - የአመጽ-አልባ ወይም የወታደራዊ ትግል አማራጭን መከተል ይቻላል። በጣም አስፈላጊው፣ አንድ ፓርቲ አመጽ-አልባ ወይም ወታደራዊ አመራጭን በመምረጥ በአለመምረጡ ሳይሆን ስኬቱ በመጨረሻ የሚወሰነው፣ በድርጅቱ ጥንካሬ፣ በአመራሩ ቆራጥነትና ጽናትና በስትራቴጂው ውስብስብነትና ተግባራዊነት ምክንያት ነው። ኦነግ ወታደራዊ ትግል በመምረጡ ተሳስቷል ብለው ፕ/ር መሳይ ማመናቸው አስደንቆኛል፤ ግና ሌሎች ድርጅቶችን በተመሳሳይ እንድያ ለማለት ተስኗቸዋል፤ ለምሳሌ በቅርቡ የምርጫ አብዮት ከሞከረ በኋላ አገዛዙ በማንኛም አስፈላጊ አማራጭ መወገድ አለበት ብሎ የደመደመው ግንቦት 7 ካልተጠቀሱት አንዱ የሚጠቀስ ነው።

## የተሳሳተ ግምት ወይስ?

ፕ/ር መሳይ «መሀል ሰፋሪ» ከሚባሉ ጥቂት ምሁሮች አንዱ መሆኑንና የራስን እድል በራስ የመወሰንና የመገንጠል ርዕዮተ-ዓለም ፖለቲካን በመቃወም ወቅታዊና አመክንዮአዊ ጭብጦችን የሚዳስስ ምሁር መሆኑን በደንብ ማወቄን ላሳውቅ እወዳለሁ። በቀርብ ባወጣው ጽሁፉ እንኳን፣ አብላጫ ቁጥር ያለው ብሔር ለመገንጠል መጠየቁ «ራስን-የሚያሳንስ» ነው የሚለውን ተቀባይነት ያለውን ክርክሩን አንስቷል።

ነገር ግን እንደአለመታደል፣ እንደሌሎቹ መሀል ሰፋሪ ምሁራን፣ ፕ/ር መሳይ ጥናቱን የፃፈው የኦሮሞን ጥያቄ የማቀነቀን ኦሮሞ በመሆኔ ብቻ እኔን ተገንጣይ አድርጎ በመገመት ነው። ይህ መከራከሪያው የጽሁፌን ዋና መልዕክት ከመረዳት የጋረደው ይመስላል - በተለይ መደምደሚያዬን።

በተጨማሪ፣ የኦሮሞ መብትን በማቀንቀኔ ምክንያት ብቻ ፕ/ር መሳይ እኔን ገንጣይ አድርጎ ፈርጆኛል። ለምሳሌ፣ «እኛ ኦሮሞዎች ችግራችንን ለመቅረፍ የሚያስችሉን ባሕሎች፣ ኃብቶችና ፅናት ያለን መሆናችን ብቻ ሳይሆን፣ ጠቅላላውን ምስራቅ አፍሪካን ዴሞክራሲያዊ ለማድረግ፣ ለማረጋጋትና ለማልማት ተቀዳሚውን አስተዋፅኦ ማበርከት እንችላለን፣ ግዴታችንም ነው።» ብዬ ብጽፍም፣ እርሱ ግን፣ ለጃዋር ***ሉዓላዊት ኦሮሚያ፣*** «ችግራችንን ለመቅረፍ የሚያስችሉን ባሕሎች፣ ኃብቶችና ፅናት ያለን መሆናችን ብቻ ሳይሆን፣ ጠቅላላውን ምስራቅ አፍሪካ ዴሞክራሲያዊ ለማድረግ፣ ለማረጋጋትና ለማልማት ተቀዳሚውን አስተዋፅኦ ማበርከት እንችላለን፣ ግዴታችንም ነው።» በማለት ደምድሟል። እንዴት ሆኖ የእኔ አረፍተ-ነገር ገነጣጣይ ይሆናል፣ እርሱ ***«ኦሮሞ ኢትዮጵያን ዴሞክራሲያዊ ለማድረግና ለማጠንከር የሚችል ኃይል ሊሆን ይችላል።»*** ብሎ ከእኔ ጋር በተመሳሳይ የደመደመው ድምዳሜ እያለ ሳለ።

**መደምደሚያ**

በኦነግ ላይ ጽሁፌን ስጽፍ፣ የተወሰኑ ኦሮሞዎችና ብዙ ኦሮሞ ያልሆኑ፣ የኦነግ ቀውስ የመነጨው ከተከተለው ርዕዮተ-ዓለም ነው ብለው እንደሚያምኑ አውቅ ነበር:: ድርጅቱ ለመከፋፈሉና ለመዳከሙ፣ «መነሻ» ግቡን - ሉዓላዊት አገር መመስረት - በመተዉ ላይ የተወሰኑ ያሳብባሉ:: ሌሎች፣ እንደ ፕ/ር መሳይ አይነቶቹ፣ ኦነግ ርዕዮተ-ዓለሙን ሙሉ በሙሉ መተውን አለመቀበሉ በድክመቱ የሚሳበብ ነው ብለው ይገምታሉ:: ሁለቱም እነዚህ ግመቶች ሁለት ወሳኝ ግና የተለያዩ ጭብጦችን በመቀላቀል ዋና ነጥቡን ይስታሉ፤ የመጀመሪያው፣ ርዕዩተ-ዓለም ለድርጅቱ መዳከም ምክንያት መሆን/አለመሆኑ ሲሆን ሁለተኛው፣ ርዕዩተ-ዓለሙ የኦሮሞን ትግልና የኦሮሞን የአጭርና የረዥም ጊዜ ጥቅሞች ለማስጠበቅ ብቁ ነው/አይደለም) የሚለው ነው:: እላይ እንዳብራራሁት፣ የአንድ ሽማቂ ዋና ግብ አንድን አገዛዝ ማሽነፍ እስከሆነ ድረስ፣ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን ርዕዩተ-ዓለም ትርጉም ያለው እንቅፋት አያስከትልም ወደሚል መደምደሚያ ደርሻለሁ:: እርግጥ ነው፣ አማፂዎች ቁጣዎችን እጅግ ውጤታማ አብዮታዊ ኃይል ሊሆን ወደሚችል ብሔርተኝነት ለመለወጥ እንዲረዳቸው አድርጎ አዎንታዊ አስተዋጽኦ ይጫወታል ብሎም ጠንካራ ክርክር ማድረግ ይቻላል::

ሆኖም፣ ርዕዮተ-ዓለም ሕዝብን ለማደራጀት ነገሮችን ቀላል ያደርጋል ማለት፣ ከነፃነት በኋላ ያለውን የአጭርና የረዥም ጊዜ ውጤቶች በጥንቃቄና በአመክንዮዓዊ አቀማመር ሳይቃኝ መተግበር አለበት ማለት አይደለም:: ስለዚህም፣ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን ወይም የመገንጠል አጀንዳ ሙግት፣ ኦሮሞንም ሆነ ሌሎች ብሔሮችን ወደፊት የሚጠቅማቸው አይደለም የሚለው ተቀባይነት ያለው ነው:: ሆኖም፣ ለድርጅታዊ ድክመት ርዕዮተ-ዓለምን ተጠያቂ ማድረግ ግን ተጣራሽ ነው::

# አሸናፊው ማነው?

**በመሳይ ከበደ (ፕሮፌሰር)**

ጃዋር ሲራጅ መሐመድ «ኦነግ፣ የርዕዮተ-ዓለም ወይንስ የአመራር ክስረት?» /«The OLF: Ideological or Leadership Bankruptcy?» የተሰኘውን ጽሁፌን በተመለከተ ላሳየኝ መልካምነት ላመሰግነው እወዳለሁ:: ለዚህ ጽሁፌ አሳማኝ መከራከሪያ ነጥቦች የማቅረብ አስደንጋጭ ድክመታቸውን ብቻ ሳይሆን በጉዳዩ ላይ እንኳን ለመወያየት አለመፍቀዳቸውን

ጭምር በሚያሳይ መልኩ ብዙ የኦሮሞ ተወላጆች ስሜታዊ ምላሾችን እና ግላዊ ጥቃቶችን ያዘለ መልስ ሰጥተዋል:: እንዲያውም አንዳንዶች ኦሮሚያ ሌላ የውጭ አገር እንደሆነች ሁሉ የኦሮሞ ጉዳይ እንደማይመለከተኝ እስከመግለጽ ሁሉ ደርሰው ነበር:: ጃዋር ለኦሮሞ እንቅፋት የሆነው ርዕዮተ-ዓለም ሳይሆን አመራር መሆኑን ለማሳየት መፈለጉ እና መከራከሩ አስደሳቹ ልዩነት ነው:: የጃዋር ጠንካራ ምላሽ የውይይት መከፈትን የሚያመላክት ስለሆነ እኔ ደግሞ ከዚያም በበለጠ ለረጅም ጊዜ የሚቆይ ወዳጅነትን ባነገበ መልኩ የሚከተለውን እላለሁ::

በቅድሚያ በጃዋር መከራከሪያ ነጥቦች ልጀምር:-

*1). እጅግ አብዛኛው የኦሮሞ ህዝብ የኦነግን የብሔርተኝነት አጀንዳ ስለሚደግፍ የርዕዮተ-ዓለም ክስረት የለም:: 2). ኦነግ የሚንቀሳቀሰው ለትጥቅ ትግል ሰርጎ ገብ ምቹ ባልሆነ መልክዓ-ምድራዊ ሁኔታዎች እንደሆነ መናገር ከእውነት የራቀ ነው:: 3). የህወሓት እና የሻዕቢያ ስኬት የአመራርን አስፈላጊነት ይጠቁማል:: 4). የኢሕአፓ ሽንፈት በርዕዮተ ዓለም ምክንያት ከመሆኑ ይልቅ በአመራሩ ስትራቴጂካዊ ስህተቶች ነበር::* የሚሉ ናቸው::

ከነዚህ መከራከሪያ ነጥቦች መረዳት የምንችለው «ርዕዮተ-ዓለም የሰርጎ ገብን ሽንፈት እና ስኬት በመወሰኑ ረገድ ያን ያህል ሚና የማይጫወት» መሆኑን ነው:: አንድ ድርጅት ደጋፊ ማሰባሰቢያ ርዕዮተ-ዓለሙን እርግፍ አድርጐ መተዉ ራስን ማጥፋት በመሆኑ ምክንያት ሰርጎ ገቡ በጥንካሬ ብቁ እስኪሆን ድረስ የማሻሻያነት አማራጮችን ከግምት ማስገባት እንደማይችል ጃዋር ጨምሮ ያስረዳል:: በሌላ አገላለጽ የኦሮሞ የብሔርተኝነት ወይም የተገንጣይነት አጀንዳ ንቅናቄው ራሱን ለማሻሻል ብቁ እስከሚሆን ጊዜ ድረስ ተጠብቆ መቆየት አለበት::

የኦሮሞ ህዝብ የኦነግን የተገንጣይነት አጀንዳ ይደግፋል ብሎ መናገር እውነት ነውን? ያንን ለመመልከት ጉዳዩን እናስፋውና የኤርትራ ህዝብ የሻዕቢያን የመገንጠል ግብ ደግፎ እንደሆን፣ እንዲሁም የትግራይ ህዝብ በኤርትራ መገንጠል እና የኢትዮጵያን በኃሳ መስመሮች መከፋፈል የተስማማ ስለመሆኑ እንጠይቅ:: ሁለቱም ንቅናቄዎች ወደ አምባገነናዊ ሥርዓቶች ያመሩ ከሆነ ህዝባዊ ድጋፍ የሚባለው ነገር እንወክለዋለን የሚሉት ህዝብ ላይ በግዴታ ተጭኖ የነበረ በመሆኑ ምክንያት አይደለምን? ኤርትራዊያንም ሆኑ የትግራይ ህዝቦች ራስ ገዝነትን (Self-rule) መፈለጋቸው እውነት ነው፤ ነገር ግን ማዕከላዊነትን መዋጋት አንድ ነገር ሲሆን መገንጠልን ማቀንቀን ደግሞ ሌላ ነገር ነው:: የኋለኛው (መገንጠልን ማቀንቀን) በምዕራቡ ዓለም የተማሩ ኢትዮጵያዊያን በህዝቡ ስም የመናገርን መብት በተቆጣጠሩበት ጊዜ የነበረው የ60ዎቹ ዘመን ልሂቃዊነት ዳግም ውልደት እንጂ ሌላ አይደለም::

ለመገንጠል ህዝባዊ ድጋፍ ማግኘትን በተመለከተ ጃዋር እራሱንም ሆነ ሌሎች ኢትዮጵያዊያንን ሊያሳምን የሚችልበት ብቸኛው መንገድ ጠንካራ ማሻሻያዎችን በማካሄድ የሚጀምረውን ነፃ እና ፍትሃዊ ዴሞክራሲያዊነትን ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡ ሥልጣን በመጋራት እና በዴሞክራሲያዊ ግንኙነቶች የተወሰነ ጊዜ ካለፈ በኋላ የኦሮሞ ህዝብ አሁንም የመገንጠል ፍላጐቱን ከገለፀ፣ ያን ጊዜ ብቻ ነው ስለህዝባዊ ድጋፍ መናገር የምንችለው፡፡ ሆኖም ጐሰኝነትን እና ብሔርተኝነትን በአንድነት የሚያጣምሩትን (ethno nationalists) ጨምሮ ሁሉም የጽንሰ ሀሳብ ፈጣሪዎች በእውነተኛ የዴሞክራሲ መዋቅር ውስጥ የመገንጠል እድል የጠበበ ስለመሆኑ ያውቃሉ፡፡ በሌላ መልኩ ሲቀመጥ ጃዋር እንደ እውነታ ያቀረበው ገና እውነታ አልሆነም፤ ይህ መከፋፈልን ለማረጋገጥ ያለሩ አሳግባብ በደሎችን የሚጠቀም የልሂቃን ብዝበዛ (ተፅዕኖ) ነው፡፡

በርግጥም የኦሮሞ ህዝብ ከተቀረው የአገሪቱ ክፍል መነጠል ፈልጐ ከነበረ በዓለም ላይ የትኛውም ኃይል ሊያስቆመው እንደማይችል ጨምሬ እገልፃለሁ፡፡ ታዲያ የጃዋር ጥድፊያ ምንድነው? ዴሞክራሲ እንዲሰፍን ይሁንና በደሎቹ አሁንም እውን ሆነው ከቀጠሉ የፈለግከውን ታገኛለህ፡፡ በነገራችን ለይ ጃዋር «ሁሉንም ኦሮሞዎች በአንድ ርዕዮተ-ዓለም ስር እና በአንድ ድርጅት ስር በመመደብ» እኔን ሲወቅሰኝ ኦነግ የኦሮሞ ህዝብን በመወከል ረገድ የብቻ ቁጥጥር (monopoly) እንደሌለው ያምናል፡፡ ምንም እንኳን እስከዛሬ የፃፍኳቸው መጽሐፎች እና መጣጥፎች ለኢትዮጵያ አለመሰልጠን የማዕከላዊ ሥርዓትን እንደዋና ምክንያት አድርገው የሚያስቀምጡ ቢሆንም፡፡ የኔን አቋም "centrist" (የማዕከላዊነት አቀንቃኝ) ሲል የጠራበት ደግሞ ሌላው አጋጣሚ ነው፤

## አፐሎችን ከብርቱካኖች ጋር ማነፃፀር

ኦነግ የሚንቀሳቀሰው ለሰርጎ ገብ ምቹ (ደጋፊ) በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ የመሆኑን የጃዋርን ግምት እንዳለ እተወዋለሁ፤ ምክንያቱም ይህ አሜሪካ ሆነው በሚጽፉ ሰዎች ሊወሰን አይችልምና፡፡ ሆኖም ፖለቲካዊ እና ወታደራዊ ድጋፎችን የሚያቀርብ፣ በተለይም እንደመጠለያ ሊያገለግል የሚችል አጐራባች አገር የመፈለጉ ጉዳይ ሳይነሳ አይቀርም፡፡ ጃዋር በመጀመርያ ጽሁፉ በአጽንዖት እና በትክክል የተቃወመውን፣ ማለትም እየጨመረ የመጣው የኦነግ የኤርትራ መንግስት ጥገኛ መሆንን ጉዲ ውጤት በምላሹ ላይ ሙሉ ለሙሉ ቸል ብሎታል፡፡ እናም የትጥቅ ትግልን ወደመምረጡ ያመራው የመገንጠል ርዕዮተ-ዓለም ለጥገኝነቱም ተጠያቂ ነው፡፡

ኦነግ ተስማሚ መልክዓ-ምድራዊ ሁኔታዎች አሉት ከተባለ ጥያቄው ለምን አሁንም ድረስ እንደከሸፈ (እንደተሰናከለ) ሆነ የሚለው ነው:: የጃዋር መልስ ግልጽ ነው:- የአመራሩ ከባድ ድክመቶች:: ነጥቡንም ለማስረገጥ የማነፃፀርያ መንገድን ተጠቅሟል፤ በተጠቃሽም ህወሓት እና ሻዕቢያ በደርግ ላይ ያገኙት ወታደራዊ ስኬት:: ይሁንና ግን ንጽጽሩ ከተለያዩ አቅጣጫዎች እንከንን ያዘለ ነው:: ማንም ሰው የኤርትራን መገንጠል ከኦሮሚያ ጋር ሊያነፃጽረው አይችልም:: የተለያዩ ታሪካዊ እና መልክዓ-ምድራዊ ምክንያቶች ጣልቃ መግባታቸው ብቻ ሳይሆን በኤርትራ ጉዳይ ላይ እንደነበረው ሁሉ አናሳ ቡድኖች ብዙውን ጊዜ ከመገንጠል ውጪ ሌላ ምርጫ የላቸውም::

ወደ ኦሮሚያ ስንመጣ የምንመለከተው፣ ምንም እንኳን የአገሪቱ ትልቁ የጐሳ ቡድን እንደሆነ ቢገልጽም የአንድ መገጠልን የሚፈልግ ቡድን ያልተዳኘ ጉዳይን ነው:: የጉዳዩ ተግባራዊነት የጐደለው መሆን ነው ስለ የርዕዮተ-ዓለም ክስረት እንድናገር የገፋፋኝ:: መገንጠል ሁሌም ቢሆን የግዞት ጠያቂ ሰዎች ርዕዮተ-ዓለም ነውና በታሪክ መዛግብት ውስጥ አብላጫነት ያላቸው ቡድኖች ለአገር ሲቆሙ ቆይተዋል:: ለዚያም ነው ስለ «ራስን ማቁሰል»/"Self-mutilation" የተናገርኩበት ምክንያት፤ ይህም አንድ ቡድን ልክ ተስፋ እንደቆረጠ አናሳ ቡድን ወደማሰብ እና መንቀሳቀስ ዘቅጧል:: የኦሮሞ ህዝብ ከእምቅ አቅሙ ጋር የሚስተካከል ርዕዮተ-ዓለም ይፈልጋል:: ያን ጊዜ ብቻ ነው አሸናፊዎች ሊሆኑ የሚችሉት::

**አሸናፊው ማነው?**

ህወሓትን በተመለከተ፣ ትግራይ በታሪክም ሆነ በባህል ከኢትዮጵያ የማዕዘን ድንጋዮች አንዷ እንደመሆኗ ያገኘው ስኬት ከማጣጣሚያ ጭብጥ ጨው ጋር መወሰድ አለበት:: በዚህም የኢትዮጵያን መከፋፈል የሚደግፍ ማንኛውም ርዕዮተ-ዓለም የትግራይን ህዝብ ታሪካዊ ሚና እና ማንነት የሚፃረር ነው:: ለዚያም ነው የህወሓትን ድል ማድረግ በተመለከተ በሰማሁኝ ቁጥር ግራ መጋባቴን መቋቀም የማይቻለኝ:: የህወሓት ስኬት በኤርትራ መገንጠል ላይ የተመረኮዘ ከነበረ ድሉ የቱ ጋር እንደሆን አይታየኝም:: መንግስቱ ኃይለ ማሪያምም ኤርትራ እንድትገነጠል ፈቅዶ በሥልጣን መቆየት በቻለ ነበር:: እንዲያ ያለ ውጤት እንደ ድል ሳይሆን እንደ ሽንፈት መቆጠር ነበረበት:: በተጨማሪም የኢትዮጵያ በጐሳ መስመሮች መከፋፈል እንዴት የድል መገለጫ ይሆናል? ኢትዮጵያ በአነሰችበት እና ለመበታተን በቀረበ ሁኔታ ውስጥ በተዳረገች ጊዜ ለትግራይ ህዝብ ድል መጣ ብዬ አልጮህም::

የትኛውም የወታደራዊ ክህሎት መጠን ኢትዮጵያ ባህር በር የለሽ ሀገር የመሆኗን ግልጽ እውነታ ማስወገድ እንደማይችለው ሁሉ በድል ፈንታ ሽንፈት ይታየኛል፡፡ ከዚህ ቀደም፣ ማለትም ቀይ ባህር በሙስሊም ኃይሎች ቁጥጥር ስር ከመሆኑ አንስቶ የኢትዮጵያ ዋናው የድክመት እና የመገለል ምንጭ የነበረው (ለህወሓት ምስጋና ይግባውና) ዳግም ተመልሷል፡፡ ከኤርትራ ጋር ዘላቂ ጦርነት የማድረግ ትርጉም ብቻ ስለሚኖረው ኢትዮጵያዊያንን አሰብን እንዲተዉት የጠየኩበትን መጣጥፍ ከተወሰኑ ዓመታት በፊት አስነብቤ ነበር፡፡ የተሻለው አማራጭ በሆነ ዓይነት የፌዴራል አወቃቀር የኤርትራ መመለስ ላይ አተኩሮ መስራት እንደሆነ ጠቁምያለሁ፡፡ አሁን የህወሓት/ኢሕአዴግ መንግስት ባህር በር የለሽ የመሆንን ግዙፍ እንከን ሙሉ ለሙሉ እየተመለከተ ነው፡፡ የጐሳ አመለካከት እና ኤርትራን በመሰዋት ጭምር ሁሉም ዋጋ የተከፈለበት ድል በአንድነት በኢትዮጵያ ከፍተኛ ጉዳት እና ተስፋ መቁረጥ አስከተሉ፡፡ ከእነዚህ እጅግ ከፍተኛ ወጪዎች (ዋጋዎች) አንፃር በትክክል «ድል» የሚለው አግባብ ያለው ቃል ነውን?

## ርዕዮተ-ዓለም እና የመተግበሪያ አማራጭ

«ርዕዮተ-ዓለም የአንድን ሰርጎ ገብ ሽንፈት እና ስኬት አይወስንም» የሚለው የጃዋር አባባል ግር አሰኝቶኛል፡፡ ስትራቴጂካዊ አማራጮች በርዕዮተ-ዓለማዊ ማነቃቂያዎች ላይ የተመረኮዙ መሆናቸውን እያወቅን ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? ኦነግ እና ሻዕቢያ ባነገቡት የተገንጣይነት ርዕዮተ-ዓለም ሳቢያ የሽምቅ ውጊያን መረጡ፡፡ ተከትሎም ከኢትዮጵያ የተቃዋሚ ኃይሎች ጋር ጥምረት ፈጠሩ፣ እናም ከኢትዮጵያ ተራማጅ (progressive) ኃይሎች ጋር መስራትን አልፈቀዱም፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ከሻዕቢያ ጋር ለማበር ህወሓት እንደ አንድ ህዝብ የትግራይ ርዕዮተ-ዓለምን መፍጠርና የጐሳ ማጣቀሻዎችን እንደከፍተኛው የፖለቲካ ትግል ማካሄጃ መቀበል ነበረበት፡፡ ይህ ርዕዮተ-ዓለማዊ አካሄድ ስለምን ከኢሕአፓ እና ከሌሎች ተራማጅ ኃይሎች ጋር መጣመር እንደተሳነው ያስረዳል፡፡ በምትኩም ወታደራዊ እና ፖለቲካዊ ድጋፍ በተለዋጭ ለማግኘት ኤርትራ ነፃ እንድትወጣ እገዛ ወደሚያደርግበት አቅጣጫ አመራ፡፡ የህወሓትን «ድል» ጥምረቱ ሳይጠቀስ፣ ይቅርታ በሻዕቢያ ላይ የነበረው ጥገኝነት ሳይጠቀስ ማስረዳት አይቻልም፡፡ በአጭሩ፣ ራዕይ ስትራቴጂንም ሆነ የቁርጠኝነት መጠንን ይቆጣጠራል፡፡

የኢሕአፓን ሽንፈት በአመራሩ ድክመት ማስረዳት ትክክል ነው፤ አመራሩ የተሰናከለው በርዕዮተ-ዓለማዊ ጽንፈኝነት ምክንያት ስለመሆኑ ከታከለበት፡፡ የድርጅቱ ዋነኛ ስህተት ተደርጐ የሚታመነው የከተማ ሽምቅ ውጊያ ትግል አማራጭ ህዝባዊ መንግስትን

እና ሶሻሊዝምን ከሚጠይቁ መፈክሮች የሚነጠል አይደለም። ኢሕአፓ ለመደራጀት እና ሀሳብን ለመግለጽ ነፃነት፣ ብሔራዊ የእርቅ መንግስት ለመመስረት፣ እና ለመሳሰሉት በዴሞክራሲያዊ ትግሎች ላይ አተኩሮ ቢሆን ወደተሳሳተ የከተማ ህቡዕ ትግል አይገባም ነበር። ከጃዋር ገለፃ በተፃረረ መልኩ፣ በወቅቱ ቢሮክራቲክ ልሂቃኑን ጨምሮ አርሶ አደሩ፣ ሰራተኛው፣ እና የአማራ ህዝብ ከተማሪዎች እና ከምሁራኑ የሶሻሊስት ርዕዮተ-ዓለም በተቃራኒ ዴሞክራሲያዊ ፍላጐቶችን አሳይተዋል። ኢሕአፓ እና ሌሎች ግራ ዘመም ንቅናቄዎች ራዕያቸውን በህብረተሰቡ ላይ ለማስረጽ እንዲመቻቸው ለመንግስት ቁጥጥር ታገሉ። ደርግ አንዳንድ ጸሐፊዎች እንደሚሉት በሲቪል ግራ ዘመሞች በመገደዱ ምክንያት ሳይሆን ሶሻሊዝም ከአምባገነናዊ ፍላጐቶቹ ጋር ስለተጣጣመለት ፕሮጀክቱን አደናቅፎ ሶሻሊምን ተቀበለ።

በኢትዮጵያ የተማሪዎች ንቅናቄ ውስጥ ከመደብ ፍላጐት ይልቅ በብሔራዊ ጥያቄ ቀዳሚነት ላይ የነበረው ክርክር የህወሓት እና የኦነግ መመስረትን ያስከተለ ቁልጭ ያለ የርዕዮተ-ዓለም ፍትጊያ ነው። በስታሊኒስት ራዕይ መሠረት ከሌሎች ቡድኖች ጋር አንድነት ከመመስረት ይልቅ የጎሳ ቡድንን ነፃ ማውጣት ቀዳሚነት አለው። የዚህ አመክኒዮ ጉጂ ውጤት በአሁኒቷ ኢትዮጵያ ላይ መሉ ለሙሉ ተላልፏል፤ በጐሳ ርዕዮተ-ዓለም የከፋፋይነት አስተዋጽዖ ተሸርሽሮ በአሁኑ ሰዓት የሞተ ቢሆንም። ይህ ሞት ርዕዮተ-ዓለም እነዴት በከፍተኛ ሁኔታ ሊሰናከል እንደሚችል ግልጽ ማሳያ ነው። እና ለጃዋር የማስተላልፈው መልዕክት ግልጽ ነው፡- አስሮ የያዘህ በአማራ፣ በአቢሲኒያ እና በኢትዮጵያ፣ እና የኦሮሞ ቅኝ መገዛት ተያያዥ ሂደት ላይ የሚሰጠው መራር ትችት ነው፤ ይህም ሂደት የጋራ ግብዎች እና ተግባሮች መፀነስን ይሸረሽራል።

የጃዋር ምላሽ የራስን እድል በራስ መወሰን እና መገንጠል ጥቅም ላይ የዋሉት እንደመሰረታዊ ጠቀሜታ ሳይሆን ለመቀስቀሻነት እንደሆነ የሚጠቁም ይመስላል። እንዲህም ይላል፡- «አንድ ርዕዮተ-ዓለም ድጋፍ ማሰባሰብን ቀላል በማድረጉ ምክንያት ብቻ ከነፃ መውጣት በኋላ ለሚከተሉ የአጭር እና የረጅም ጊዜ ውጤቶች ላይ ጥንቃቄ የተሞላበት እና ምክንያታዊ ግምገማ ሳይደረግበት ተቀባይነት ማግኘት አለበት ማለት አይደለም።» ታክቲካዊ ዓላማ ብቻውን የመቀስቀስ ጉልበትን ይሸረሽራል፡- የተገንጣይነት ርዕዮተ-ዓለም ህዝቦችን ከመከፋፈሉ በተጨማሪ ታክቲካዊ ጥቅም ማለት አመራሮቹም በሚሰብኩት ርዕዮተ-ዓለም አያምኑም ማለት ነው። ጉዳዩ ያ ከሆነ ደጋፊውን እና ተቃዋሚውን መዝኑት፤ እናም የተሻለው አማራጭ ርዕዮተ-ዓለሙን ከነጭራሹ ማስወገድ መሆኑ ግልጥ ይሆናል።

ሆኖም ጃዋርም ሆነ የኦነግ አመራሮች ርዕዮተ-ዓለሙን ለመተው ፈቃደኞች አይደሉም። ለምን? ምክንያቱም ጽንፈኛ ቡድኖች ተነስተው የአሁኑን አመራር ከጨዋታ ውጪ እንዲያደርጉት ይፈቅዳልና። ይህ እንዲህ ዓይነት ከፋፋይ ርዕዮተ-ዓለምን ለረጅም ጊዜ

ለማብቀል እና ለማስራጨት አይቀሬ ክፍያ ነው:: የሆነ ቦታ ላይ አቅጣጫ መቀየር የማይቻልበት ሁኔታ ተፈጥሯል:: ሀገሪቱን ቁርጠኝነት የሞላበት የዴሞክራሲ ሥርዓት መንገድን ለማስያዝ ከኢትዮጵያ ለዘብተኛ እና ተራማጅ ኃይሎች ጋር ህብረት የመፍጠሪያ ሁሉም ምክንያቶች የጽንፈኛ ቡደኖችን መነሳት ሊገድቡ ይችላሉ::

/ፕሮፌሰር መሳይ ከበደ፣ በኦሐዮ ዴይተን ዩኒቨርስቲ የፍልስፍና መምህር ሲሆኑ ከአምስት ያላነሱ መጻህፍት ደራሲም ናቸው:: ከመጽሐፎቻቸው ውስጥ Radicalism and Cultural Dislocation in Ethiopia; እንዲሁም Africa's quest for a Philosophical Decolonization ተጠቃሾች ናቸው/

# ጥቂት ነጥቦች ስለዴሞክራሲ

**በግዛው ለገሠ**

"The ballot is stronger than the bullet" ወይንም «ኮሮጆው ከጥይት የበለጠ ጠንካራ ነው» በማለት 16ኛው የአሜሪካ ፕሬዝዳንት አብርሃም ሊንከን በኢሊኖይ፣ ብሉሚንግተን የተናገሩት ስለዲሞክራሲ ነበር:: በርግጥም ዲሞክራሲ የአስተዳደር ሥርዓት ስለመሆኑና በዓለም ላይ ካሉና ከነበሩ ሥርዓቶች የተሻለው ተደርጐ ስለመወሰዱ ብዙ ተብሏል:: ሆኖም የዲሞክራሲ ሥርዓት ላይ ያነጣጠሩ አያሌ ጥያቄዎች ከተለያዩ ቦታዎች ይሰነዘራሉ:: ዓለም አቀፉ የፓርላማዎች ሕብረት የዲሞክራሲን ምንነት፣ ከዲሞክራሲ ጋር ተያይዘው ለሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽ፣ እንዲሁም በዲሞክራሲ ሥርዓት የፓርላማን ወሳኝነትና የሚጫወተውን ሚና ለማስገንዘብ በድረ-ገጹ ያሰፈራቸው አያሌ ቁምነገሮች አሉ:: እኛም ከነዚህ ቁምነገሮች የተወሰኑትን በመውሰድ፣ በተለይም ለዲሞክራሲ ትግበራ እንደችግር የሚቆጠሩትን ጉዳዮች እና አማራጭ መፍትሔዎች ለዛሬ ጽሁፋችን እንደሚከተለው አሰናድተናቸዋል::

## «ህዝብ» እነማንን ይወክላል?

ዲሞክራሲ የህዝብ መንግስት፣ በህዝብ የሚመራ መንግስት፣ እና ለህዝብ የቆመ መንግስት የሚያራምደው ሥርዓት ነው:: ነገር ግን «ህዝብ» እነማንን ይወክላል? በዴሞክራሲ የጥንስስ ዘመን ሴቶችን፣ አሽከሮችን እና የሌላ ሀገር ዜጋ ነዋሪዎችን በማግለል የዜግነት መብቶች በከፍተኛ ሁኔታ የተገደቡ ነበሩ:: ከዚያም በኋላ ቢሆን የመምረጥ መብት በተመሳሳይ ሁኔታ ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ የተፈቀደ ነበር:: ይህ መሰረታዊ መብት ለሁሉም አዋቂ (ለአቅመ አዳም የደረሱ) ሴቶች እና ወንዶች የተሰጠ ለመሆን ክፍለ ዘመናት የፈጀ

ትግልን ጠይቋል፡፡ የመምረጥ መብት በአግባቡ ተግባራዊ ሲሆን ብቻ ነው የውክልና ሥርዓትን «የህዝቦች መንግስትን የመቆጣጠር» እና «በፖለቲካ ውስጥ የመሳተፍ መብትን በተመለከተ የዜጎች እኩልነት» የተሰኙትን ሁለት መርሆዎች ያቀፈ ሙሉ ዲሞክራሲያዊ ብለን ልንጠራው የምንችለው፡፡

## «ነፃ እና ፍትሃዊ» ምርጫዎች

ምርጫዎች በህዝብ ስም ውሳኔ የሚያሳልፉትን ለመምረጥ እና ለውሳኔያቸውም ተጠያቂነትን ለማስረፅ መሠረታዊ የዲሞክራሲ አሰራርን ይወከላሉ፡፡ ምርጫዎች ትክክለኛ የህዝቦች ፍላጐት (ፈቃድ) ነፀብራቅ ይሆኑ ዘንድ ድምፆች በእኩል መቆጠር አለባቸው፣ እጩዎች በነፃነት መቀስቀስ አለባቸው፣ እንዲሁም ለገዥውና ለተቃዋሚ ፓርቲዎች የተደላደለ የመጫወቻ ሜዳ ሊኖር ይገባል፡፡ የእነዚህ መርህዎች አብዛኛው ጥሰት የሚከሰተው ገዥ ፓርቲዎች ወይም መሪዎች ሊሸነፉ የሚችሉበትን እድል ሊቀበሉ በማይፈቅዱበትና ያም እንዳይፈጠር በሚከላከሉበት ጊዜ ነው፡፡

ይሁንና ግን ምርጫዎችን ማካሄድ ዲሞክራሲን አይገነባም፡፡ ህዝቦች ተከታታይነት ባለው መንገድ ተወካዮቻቸው ላይ ተፅዕኖ የማሳደርና በጋራ ጥቅሞች ላይ ከሌሎች ጋር የመገናኘት እና የመደራጀት አቅም ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ይህም ለግለሰብ መብቶች እና ነፃነቶች ጠንካራ ዋስትናን ይጠይቃል፤ በተጠቃሽም ሀሳብን የመግለፅ፣ ማህበር የመመስረትና የመሰብሰብ ነፃነቶች፡፡ ተያይዞም እነዚህን ተግባራዊ ለማድረግ ገለልተኛ የፍትህ አካል አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም የባለስልጣኖችን ተግባራት በተመለከተ ገለልተኛ መረጃ መኖሩን ለማረጋገጥ የህዝቡን ጥቅሞች ለማስጠበቅም ሆነ ለማስተዋወቅ በዜጐች መካከል መገናኘትን እና መደራጀትን ለማበረታታት ነፃ የመገናኛ ብዙሃን መገኘቱ ወሳኝ ነው፡፡

## ዲሞክራሲ ለህይወታችን ምን ዓይነት ለውጥ ያስከትላል?

ዲሞክራሲ በወታደራዊ ቁጥጥር፣ በአንድ ፓርቲ፣ በቤተሰባዊ አገዛዝ፣ አልያም በግለሰብ አምባገነናዊነት ላይ መሠረት ካደረጉ ግዞት ጠያቂ ሥርዓቶች ጋር ሲነፃጸር ለዜጐች ጉልህ ጥቅሞችን ሊያበረክት ይችላል፡፡

- መሠረታዊ ነፃነቶችን ማረጋገጥ፡፡ በዲሞክራሲ ሥርዓት ውስጥ ህዝቦች በሕግ ክበብ ውስጥ በመሆንና ሌሎችን ሳይጋፉ የፈቀዱትን ለማሰብ፣ ለመናገር እና ለማድረግ፣ እንዲሁም የእምነታቸውን ለመተግበር እና የመረጡትን ዓይነት ህይወት ለመኖር

ይችላሉ:: ሁልጊዜም ቢሆን ነፃ ህብረተሰብ ጥበባዊ ፈጣራዎችን፣ ሳይንሳዊ ግኝቶችን እና የፍልስፍና ምልከታዎችን ያበረታታል::

- ህዝባዊ ፍላጐቶችን ማርካት:: መደበኛ ህዝቦች በመንግስት ፖሊሲ ላይ የበለጠ ተጽዕኖ ባሳደሩ ቁጥር መንግስት ሀሳባቸውን እና ምኞታቸውን የማንፀባረቅና መሰረታዊ ፍላጐታቸውን የማሟላት አዝማሚያው ይሰፋል::
- ህዝቦችን በእኩል ዓይን መመልከት:: ይህ መሠረታዊ ዲሞክራሲያዊ መርህ መንግስት በፖሊሲው እና በአስተዳደሩ የህዝቦችን ፍላጐቶች ሲያሟላ አለምንም አድሎ በእኩል ዓይን እንዲሆን ይጠይቃል::
- አለመስማማቶችን ወይ ግጭቶችን በውይይት፣ በመተማመንና በመቻቻል መፍታት::

## ለዲሞክራሲ የፓርላማ አስተዋጽዖ

በህዝብ የተመረጠ ፓርላማ ወይም ሕግ አውጭ በራሱ እና በመንግስት መካከል ያለውን የሥልጣን መነጣጠል በተመለከተ ቁልፍ ዲሞክራሲያዊ ሚናን ይጫወታል:: ሕጐች በእርሱ መጽደቅ ሲኖርባቸው ሁሉም ረቂቆች ሕግ ከመሆናቸው በፊት በአጽንዖት መመርመራቸውን እና ውይይት የተደረገባቸው መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባት:: በሥልጣኑ ሚኒስትሮችን በጥያቄ በማፋጠጥ፣ መዝገቦችን በማጣራት እና የመንግስት ኃላፊዎችን በመጠየቅ የመንግስትን ሥራ ይመረምራል::

በተጨማሪም ፓርላማዎች በመንግስት ፊት እና ሕግ በማውጣቱ ሂደቱ ላይ የህዝቡን ፍላጐቶች ወክሎ በመቅረብ፣ ለሁሉም እኩል ክብር በመስጠት፣ እና በተለይም በጥልቀት በተከፋፈሉ ህብረተሰቦች የውይይት መንገዶችን በመክፈት ለመሠረታዊ መብቶች እና ነፃነቶች ጥበቃ በማድረግ ከላይ የተገለፁት የዲሞክራሲ ጥቅሞች በተግባር እውን መሆናቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው::

## የፖለቲካ ፓርቲዎች አስፈላጊነት

በሁሉም ሀገራት ማለት ይቻላል፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከሁለም ዓይነት ተቋማት መካከል እጅግ አነስተኛ እምነት የሚጣልባቸው መሆናቸውን ጥናቶች ያመላክታሉ:: ይሁንና ግን ከተወገዱ ወይም ከሌሉ እነርሱን በድጋሚ ማቋቋም አስፈላጊ መሆኑን ብዙ ሳንርቅ እንገነዘባለን:: ለዚህም ምክንያቱ በሰፊ ህብረተሰብ ውስጥ ህዝቦች አንደግለሰብ ሊያሳድሩት የሚችሉት ተጽዕኖ አነስተኛ ስለሆነ ነው፤ ድምፃቸው ይሰማ ዘንድ ከሌሎች ጋር መጣመር ይገባቸዋል:: የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ቅስቀሳ ለማካሄድ፣ የፖለቲካ ተጽዕኖ ለማምጣት እና ህዝባዊ ድጋፍ ለማሰባሰብ ተመሳሳይ አመለካከቶችን እና ፍላጐቶችን የሚጋሩ ሰዎችን

በአንድነት ያሰባስባሉ፡፡ ይህን ሲያደርጉም ወሳኝ ዲሞክራሲያዊ ተግባሮችን ያከናውናሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ፡-

- ለመራጮች ሰፊ የፖሊሲ አቋሞችን እና ፕሮግራሞችን በማቅርብ አማራጮችን ያበራክታሉ፡፡
- ፖለቲካዊ ተሳትፎን ለሚሹ በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የበኩላቸውን እንዲፈጽሙ እድል ይከፍታሉ፡፡
- ለመንግስታት አንዴ ካሸነፉ በኋላ ፕሮግራሞቻቸውን ለመተግበር ምክንያታዊ በሆነ መልኩ የተረጋጋ የፖለቲካ ደጋፊዎችን ሁኔታ ይፈጥራሉ፡፡
- ለተቃዋሚዎች እንደ አማራጭ የፖለቲካ ምንጭነት እና መንግስትን ተጠያቂ እንደማድረጊያ ተከታታይ መስፈርት ያገለግላሉ፡፡

ይሁንና ግን ዲሞክራሲያዊ ተግባሮች ህዝባዊ ድጋፍን የሚያሳጡ ጉጂ ጽንፍም አላቸው፡፡ የፓርቲ ውሳኔ የማያፈናፍን ሆኖ ሲገኝ ገለልተኛ አመለካከቶችን እና ግልጽ ውይይቶችን የሚገድብ ሊሆን ይችላሉ፡፡ ተቃውሞ ልዩነትን የሚያሰፋ ሊሆን ይችላል፤ እናም ወደ «ለመቃወም ተብሎ ብቻ የሚደረግ ተቃውሞ» ያመራል፡፡ በተጨማሪም ምርጫዎችን እና የምርጫ ቅስቀሳዎችን ለማካሄድ የሚወጣው ወጪ ሲታይ ሀብታም ግለሰብዎች እና ስፖንሰር አድራጊ ድርጅቶች ከመራጩ በበለጠ በፖሊሲ እና ሕግ በማውጣት ሂደት ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ፡፡ ይህንን ተጽዕኖ መገደብ የሚቻለው ሕጋዊ ሥልጣን ባለው በገለልተኛ ኮሚሽን በኩል ድጐማዎች እና የምርጫ ወጪዎች ላይ ገደብ በመጣል እንደሆነ ይታመናል፡፡

## የዲሞክራሲ ትግበራን በተደጋጋሚ የሚያደናቅፉ ስድስት ነገሮች

**የወንዶች ተጽዕኖ**፡፡ ከታሪክ አኳያ በብዙ ሀገራት መንግስትነት ለወንድ የተተወ ነው፡፡ አሁንም ድረስ እውነት ነው፤ እናም ከቁጥራቸው አንፃር ሴቶች ለሥልጣን የመወከላቸው እድል እጅግ ጠባብ ነው፡፡ ይህ ዲሞክራሲያዊ መርህ የሆነውን እኩልነት ከመሸርሸሩም በላይ ሴቶች ለህዝባዊ አኗኗር የሚያበረክቱትን አስተዋጽዖ ይነፍጋል፡፡

**ሙስና እና ባለስልጣናት**፡፡ ብዙውን ጊዜ ሙስና ማለት ስልጣንን ለግል ጥቅም አላግባብ ማዋል እነደሆነ ይገለፃል፡፡ ያ ሥልጣን በዲሞክራሲ ሥርዓት ውስጥ የሚተገበረው ለባለስልጣኑና ለቤተሰቡ፣ ለወዳጆቹ አልያም ለግል ግንኙነቶቹ ሳይሆን ለህዝብ ሲባል

የመሆኑን መርህ ይቃረናል:: ሙስና እየተስፋፋ በመጣ ቁጥር ህዝቡ በመንግስት ላይ ያለውን እምነትም ሆነ ለዲሞክራሲያዊ ሂደቱ የሚደረገውን ድጋፍ ይሸረሽራል::

**የአብላጫው ተጫኝነት**:: ምንም እንኳን በአብላጫ አመለካከት መሠረት የሚተላለፉ ውሳኔዎች አናሳ ቁጥር ባላቸው ከሚተላለፉት የበለጠ ዲሞክራሲያዊ ቢሆኑም፣ የግለሰብ ወይም የቡድን መሠረታዊ ዲሞክራሲያዊ መብቶችን በሚጋፉ አልያም የጐሳ፣ የቋንቋ ወይም የሀይማኖት አናሳ ቡድን ከማንኛውም የሥልጣን መጋራት በቋሚነት በተገለለበት ወቅት የጨቋኝነት ውጤት ሊኖራቸው ይችላል::

**በፓርላማው ላይ የአስፈፃሚው ቁጥጥር**:: በፖሊሲ እና ሕግ በማውጣት ሃደቱ አመራርን ማስፈን የተመራጭ መንግስታት ተግባር ነው:: ይሁንና ግን ፓርላማዎች ከብቃት ማነስም ሆነ በገዢው ፓርቲ ጥብቅ ቁጥጥር ምክንያት ከመንግስት (ከአስፈፃሚው) ተጽዕኖ ገለልተኛ ካልሆኑ የተሰጣቸውን ተልዕኮ በአግባቡ ለማከናወን ይሳናቸዋል:: ይህም በፖሊሲ እና በሕጐች ብቃት ላይ ሚና ሲኖረው የመንግስት ህዝባዊ ተጠያቂነት ይቀንሳል::

**ሚዲያ የሰፊው ህዝብ አለመሆኑ**:: በዲሞክራሲ የሚዲያ ቁልፉ መስፈርት የብዙሃን መሆኑ ነው፤ አያሌ የመረጃ ምንጮች እና የተለያዩ አመለካከቶች እና አስተያየቶች የሚስተናገዱበት:: ይህ የአመለካከት ስብጥሮሽ በሁለት አቅጣጫዎች አደጋ ላይ ይወደቃል:: በመንግስት፣ ሚዲያውን በቀጥታ በመቆጣጠር ወይም በግልጽ የማይታይ ግፊት እና ቅድመ ምርመራ በማስረጽ፤ እንዲሁም በግሉ ዘርፍ፣ የተለያዩ የሚዲያ ዘርፎችን በስፋት በባለቤትነት በመቆጣጠር::

**የህዝቡ ስሜት ማጣት**:: የህዝቡ በፖለቲካ፣ በመንግስት እና በዲሞክራሲ ሂደት እሴቶች ላይ ስሜት ማጣት ለራሱ ለዲሞክራሲ ህልውናም ከፍተኛ አደጋ ነው:: ይህ ሁኔታ ብዙውን ጊዜ በመንግስት አሰራር ላይ ጉልህ ስህተት የመከሰቱና ያንን ለመለወጥም በህዝብ ዘንድ የአቅም የለሽነት ስሜት የመንሰራፋቱ ነፀብራቅ ነው::

## ችግሮቹን ስለመፍታት

ከላይ የተጠቀሱት አብዛኛዎቹ ችግሮች በቀላሉ የሚመጣ መፍትሔ የላቸውም፤ ቀላል መፍትሔ ቢኖር እንኳን ተፈፃሚ ለማድረግ በሥልጣን ላይ ያሉት ወገኖች ተነሳሽነት አነስተኛ ሊሆን ይችላል:: ሁልጊዜ ማለት ይቻላል፣ መሻሻል የሚመጣው ከራሱ ከህዝቡ በመነጨ በተደራጀ ግፊት ነው:: በተለያዩ ቦታዎች በርግጥም ለውጥ የሚቻል ነገር መሆኑን የሚያሳዩ አያሌ የመልካም ትግበራ ተምሳሌቶች አሉ:: የዲሞክራሲ ራስን የማረም ብቃት ከመንግስት ሥርዓቶች ሁሉ የተለየ ያደርገዋል::

በኃላፊነት ቦታ ላይ የሴቶች ቁጥር መበራከት የሚመጣው በዋነኛነት የፖለቲካ ፓርቲዎች ሴቶች ከወንዶች እኩል የፓርላማ መቀመጫ የማግኘት እድል እንዲኖራቸው የእጩ አመራረጥ ሂደታቸውን እነዲለውጡ በህዝባዊ ግፊትም ሆነ በሕጋዊ መስፈርት መሠረት የመገደድ ስሜት በሚያድርባቸው ጊዜ ነው:: ሆኖም ይህ አንዱ እርምጃ ነው::

አስቀድሞ በህብረተሰቡ ውስጥ በጥልቀት የሰረጸ እንደሆን ሙስናን ለማስወገድ ቀላል መፍትሔ የለም:: የመንግስት ኃላፊዎች እና ሰራተኞች በጉቦ እና በማባበያ መንገዶች ሥልጣናቸውን አላግባብ እንዳያውሉ ብቁ ደሞዝ መክፈል ለችግሩ የአንድ ወገን መፍትሔ ሊሰጥ ይችላል:: በሌላ በኩል ጥፋተኞች የሚቀጡበትን ሁኔታ ማመቻቸት ደግሞ በሌላ ወገን ሆኖ ያገለግላል:: እዚህ ላይ ሚዲያው እና የሲቪል ማህበራት ፀረ-ሙስና ድርጅቶች ጉልህ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ::

አብላጫ ቁጥር ያለው ግለሰብዎችን ወይም ቡድኖችን እንዳይጫን ሕገ መንግስታዊ የመሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች ጥበቃ እና ሥራውን በአግባቡ የሚያከናውን ሕግ አስፈፃሚ አስተዋጽዖ ይኖራቸዋል:: አናሳ ቡድኖች ከሥልጣን መጋራቱ ጉዳይ በቋሚነት መገለላቸው በምርጫ ሥርዓት፣ በኮታ ቀመር፣ በሥልጣን መጋራት አወቃቀሮች፣ ወይም ባልተማከለ የመንግስት ሥርዓት ሊፈታ ይችላል::

ፓርላማዎች ከአስፈፃሚው ተጽዕኖ ሙሉ ለሙሉ እንዲላቀቁ በአሰራራቸው ላይ፣ በምርመራ ሥልጣናቸው ላይ ቁጥጥር ሊኖራቸው የሚያስፈልግ ሲሆን በመንግስት ላይ ሳይመረኮዙ ሥራቸውን ማከናወን የሚየስችላቸው ብቁ የሰው ኃይል እና የኤክስፐርት አቅም ሊኖራቸው ያስፈልጋል::

በመንግስት የሚደጐም የማሰራጫ ጣቢያ በመንግስት ቁጥጥር ስር መሆኑን ወይ የመንግስትን ጣልቃ ገብነት ለመከላከል በፖለቲካ የማይወሰን ወይም ለማንኛውም ፓርቲ የማይወግን ገለልተኛ ብሮድካስቲንግ ባለስልጣን መመስረት ያስፈልጋል:: የተለያዩ ሚዲያዎች በተወሰኑ ግለሰብዎች ስር እንዳይሆኑ ይህንን የሚከላከል ሕግ በግልጽ መደንገግ እንደመፍትሔ ይቆጠራል::

የህዝብን ስሜት ማጣት እና ተስፋ መቁረጥ በተመለከተ ዋናው የመፍትሔ ምንጭ በሥልጣን ላይ ያሉት መንግስታት እንደሆኑ ይታመናል:: ይኸውም ዲሞክራሲያዊ ሥርዓቱን በተግባር በማሳየት፣ የምርጫዎች አፈጻጸምን ግልጽ እና ፍትሃዊ በማድረግ፣ እንዲሁም በምርጫ ቢሸነፉ ሥልጣን ሊለቁ የሚችሉበትን አጋጣሚ ወቅቱ በደረሰ ጊዜ ተግባራዊ በማድረግ ህዝቡ ለፖለቲካ ተሳትፎ ፍላጎት እንዲያሳይ መንገድ መክፈት ይቻላቸዋል::

# ምርጫ 2002 እና የጠ/ሚ መለስ አዲሱ ስትራተጂ

ፕሬዚደንት ኦባማ፣ በተለይ በጋና ንግግራቸው፣ የአፍሪካ ገዥዎች መንግስታቸውን በቀላሉ ማሞኘት እንደማይቻላቸውና የመሪዎቹ «ፈርጣማ ገዥነት» መቀጠልን በግልጽ እንደሚቃወሙ በይፋ ገልጸዋል። በተጨማሪ፣ የአሜሪካ የውጭ ጉዳዮች ሚኒስትር /ሴክሬታሪ/ ሂላሪ ክሊንተን በጥቂት የአፍሪካ አገሮች ያደረጉት ጉብኝት ያን መልዕክት አጠናክሮ የደገፈ ይመስላል። ነገር ግን መልዕክቱ የተላለፈው አሜሪካ በቀጠናው ያላትን ጥቅሞች ባማከለ አኳኃን ነበር።

ሁለቱም ባራክ ኦባማ እና ሂላሪ ክሊንተን በጉብኝታቸው ወቅት ግልጽ ያደረጉት ንግግር፣ የአፍሪካ ገዥዎች ከ«ኦቫል ኦፊስ» የትኛውንም አይነት ይፋዊ አጋርነት የሚፈልጉ ከሆነ አስቀድመው ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ መተግበር፣ የሕግ የበላይነትን ማክበርና የሕዝባቸውን አመኔታ ማሸነፍ እንዳለባቸው ነው። የአሜሪካ የውጭ እርዳታ ተቀባዮች ከሆኑት አገሮች አንዷ የሆነችው ኢትዮጵያ፣ ከኋይት ኀውስ የተላለፈው መልዕክት የጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ አስተዳደርን አስግቶታል።

በቡሽ አስተዳደር ወቅት «በሽብር ላይ የታወጀው ጦርነት» ለጠ/ሚኒስትር መለስ የተመቸ ሆኖላቸው ነበር፤ ያልተገደበ ድጋፍም ከዩናይትድ ስቴትስ አግኝተዋል። ሆኖም ዛሬ የዋሽንግተንን ያልተከፋፈለ ትኩረት አስጠብቆ ለማቆየት አስቸጋሪ ወቅት አጋጥሟቸዋል።

የኦባማ አስተዳደር በድህረ ምርጫ 97 በተከሰቱ ግጭቶችና በሌሎች አሉታዊ የሰብዓዊ መብቶች ማሕደሮች ምክንያት፣ ብልሀት በተላበሰ መልኩ በግላጭ ከአቶ መለስ መንግስት ጋር ከመቆራኘት ራሱን ቆጥቧል። በተጨማሪ፣ አቶ መለስ ከኦባማ ጋር ደልዳላ ጉዞ እንዳይኖራቸው ያስተጓጓኳቸው አያሌ ኢትዮጵያውያን በዋሽንግተን ዲሲ አካባቢ ይገኛሉ። አብዛኞዎቹ ዲያስፖራ ኢትዮጵያውያን የአቶ መለስ አገዛዝን በእጅጉ ይተቻሉ፣ ይቃወማሉ ምክንያቱ የሚመሩት የፖለቲካ ድርጅት የአገሪቱን ኢኮኖሚና ፖለቲካ በብቸኝነት መቆጣጠሩ ነው። አሁን በቅርቡ እንኳን በአዲስ አበባ ያለውን መንግስት የሚያወግዝ የነፃነት ሰልፍ በ«ካፒቶል ሂል» ፊት ለፊት ተካሂዶ ነበር።

በቅርቡ የኢትዮ- አሜሪካን ግንኙነት አስመልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ አቶ መለስ ሲመልሱ፣ «እንኳን ከኦባማ ጋር፣ ከጸሃይ በታች ካለ ከምንም ነገር ጋር በማንስማማበት ወቅት አለመስማማታችንን በፋይ እንገልጻለን! አዎ! እንገልፃለን። ያ በየወቅቱ የውጥረት ስሜት ይፈጥራልን? አዎ ምናልባት ሊፈጥር ይችላል። ያ ማለት ግንኙነቱ መሰረታዊ

ችግር አለበት ማለት ነው? አይደለም:: እናም የተጤነ ቢመስልም ወጥረቱ አዲስ ነገር የለውም፤ ከኦባማ አስተዳደር ጋር በተያያዘ የተለየ ነገር የለም:: ምንም ከሌለ፣ የኦባማ አስተዳደር መምጣት የተወሰኑ ፍራቻዎችን አቅልሎአል ማለት ነው ማለት ይቻላል፤» በማለት የመንግስታቸውን አቋም ሞግተዋል::

በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ፖለቲካ ደህንነት መታጣት ሲጤን፣ ግልጽ አጋርነት ከጠ/ሚኒስትር መለስ መንግስት ጋር መመስረት ለፕሬዝዳንት ኦባማ ጠቀሜታ አይኖረውም:: ፕሬዝዳንት ኦባማ፣ ስልጣን ከመረከባቸው አስቀድሞ፣ ተኮልኩለው ድምፃቸውን የሰጡአቸው ዲያስፖራ-ኢትዮጵያዊያንን ጨምሮ በዓለም ያሉ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ድሀ ሕዝቦችን ያማከለ የውጭ ፖሊሲ በዋሽንግተን አመጣለሁ ብለው ቃል-ኪዳን ገብተው ነበር:: ያን ቃል-ኪዳን አለማክበር ምን የማይወጣው ሌላኛው የሕዝብን አመኔታ የማያከብሩ ፖለቲከኛ የሚያደርጋቸው ነው::

## አቶ መለስ እና ብቸኛው የፖለቲካ ድርጅታቸው

የአቶ መለስ ታማኞች አርሳቸውን «የሕዳሴ ሰው» ብለው ሊወስዷቸው ይችላሉ:: ሆኖም መንግስታቸውን ለሚቃወሙ፣ አቶ መለስ ሌላኛው «አምባ-ገነን» ናቸው:: የሚቃወሟቸው ፍራቻቸው፣ ድርጅታቸው እስከተቻለው ጊዜ ድረስ በስልጣን ላይ የሙጥኝ የማለቱ ጉዳይ ነው:: አቶ መለስ ከመወለዳቸው በፊት በኢትዮጵያ በነበሩ ለእድገት እንቅፋት በሆኑ ችግሮች - ሙስና እና ምዝበራ - የመንግስታቸውን ከፍተኛ፣ የበታችና ዝቅተኛ ደረጃ የያዙ ባለሥልጣናት ይወነጅሏቸዋል::

እውነታው፣ ድሃ ኢትዮጵያውያን በማንኛውም አይነት «አምባ-ገነንነት» መሰላቸታቸው ነው፤ ከ40 ዓመታት በላይ በቀዳማዊ ኃ/ስላሴ ንጉሳዊ ሥርዓት፣ በኮሎኔል መንግስቱ ኃ/ማርያም የ17 ዓመታት አገዛዝ እና በአሁን ከ18 ዓመታት በላይ በሥልጣን ላይ ባለው በአቶ መለስ መንግስት:: የቀጠለው ፖለቲካዊ ቀውስ መንፈሳቸውን አዳክሞታል:: ለምስቅልቅሉ ሕዝብ በከፊል ተወቃሽ ቢሆንም፣ ቀንበሩን መሸከም እጅግ አታካች ነው:: ገዥዎቹ ከገሀነም እንዲሁ በቀጥታ ጉልላት ላይ አልሰፈሩም እኮ:: ምሁራኑ እስከ 99.99 በመቶ ድረስ የምዕራቡ ርዕዮተ-ዓለሞች አቀንቃኞች ቢሆኑም፣ የወጡት ከማሕበረሰቡ ውስጥ ነው፣ የተቀረፁትም በባሕሉ:: አሳዛኙ እውነታ ምንድን ነው፣ ሁሌም ሸክሙ ሕዝቡ ላይ መሆኑ ነው:: የሸሿቸው የሥልጣን ባለቤቶች ካለ ምህረት ሕዝቡን እየመዘበሩ ባለበት ሰዓት፣ ሥልጣን የከዳቸው ምሁራን የባሰው ሲባባስ ወደ አመቺ አገሮች አገራቱንና ለራሱ ራሱን እንዲታደግ መከታ የሌለውን ሕዝብ ጥለው ይሸሻሉ::

አሁን ድረስ፣ የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ፍልሚያ በርዕዮተ-ዓለም ዙሪያ መሰረቱን እንደጣለ ይገኛል፤ እንዲሁም አቶ መለስ ታጣቂ ተማሪ በነበሩበትም ወቅት ተመሳሳይ ሁኔታ ነው ያለው። ከኢኮኖሚም አንፃር፣ አንዳንዶች «ኢትዮጵያ በእርዳታ ሱስ ተጠምዳለች» እስከማለት ባደረሳቸው የውጭ እርዳታ አገሪቱ በእጅጉ ጥገኛ ነች። አቶ መለስ ኢትዮጵያን ወደ «መካከለኛው ገቢ» ኢኮኖሚ በቅርብ እለውጣታለሁ በማለት ቢከራከሩም፣ ቁጥራቸው እየጨመረ የሄደ ሕፃናት «ወላጅ አልባ» እየተባሉ ወደ ውጭ ይላካሉ። በዛሬዋ ኢትዮጵያ አብዛኛው ሕዝብ እንደ ትላንቱ ድሃ ነው፣ ከዚያ የበለጠ ባይሆን እንኳ። «መካከለኛ ገቢ» ያለው ሕዝብ ጭራሽ የለም ማለት ይቻላል። ሕዝቡ በፒራሚድ አናት ወይም ስር ግርጌ ላይ ነው ያለው። በጣም ብዙ ሰዎች የተሻለ ሕይወት ፍለጋ በረሃ ወይም ባሕር ሲያቋርጡ የበላቸው ጅብ አልጮህ ይላል። የአሜሪካ ሕልማቸውን እውን ለማድረግ «ዳይቨርስቲ ቪዛ ሎተሪ» (DV) የሚሞሉ ሰዎች ቁጥር በየዓመቱ በእጥፍ ያድጋል። ከአሜሪካ ወይም ከአውሮፓ ዩኒቨርስቲዎች የሚመረቁ አብዛኞቹ ተማሪዎች አልፎ አልፎ ነው እትብታቸው ወደ ተቀበረባት አገራቸው የሚመለሱት። አብዛኞቹ የአገሪቱ ተመራቂዎች ሥራ አጥ ሆነው ይቀራሉ። ጥቂት ሥራ ፈጣሪዎች ነው ያሉት፤ በእሲያ ሕይወቶችን የለወጠው የጥቃቅን/አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች የገንዘብ ድጎማ እጅግ በጣም በጥቂቱ ነው የሚስተዋለው። ጥቂቶች፣ ከመንግስት ጋር የወገኑ፣ ንግዶችን በብቸኝት ይቆጣጠራሉ። ይህ እረፍት የሚያሳጣ እውነታ፣ አቶ መለስ ወደ መኝታቸው ባቀኑ ቁጥር አእምሮአቸውን እረፍት የሚነሳ አይደለምን?

ትምህርት ካገባደድኩ ከ20 ዓመት በኋላም፣ ከዕርዳታ የተላቀቀች፣ ፍትሀዊ ፖለቲካ የነገሰባትና ሕዝቡ ስለውጭ አገራት ከማለም ይልቅ በትውልድ አገሩ አዎንታዊ የሆነ ነገር ለመስራት ከእንቅልፉ ሲነቃ ሁሌም ጥልቅ ፍላጎት ያደረበት፣ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ማየት እሻለሁ። በተጨማሪ፣ የወደፊት ልጆቼ በኢትዮጵያዊነታቸውና በአፍሪካዊ ማንነታቸው፣ የብሔር ውርሳቸው እንዳለ ማለት፣ እንዲኮሩ በሚያስችላቸው የተከበረች አገር እና ሕገ መንግስታዊ መብቶቻቸውን በመጠቀም ሀሳባቸውን በነፃነት መግለጽ የሚችሉበትና ካለፍራቻ መሪዎቻቸውን የሚተቹባት እንድትሆን እመኛለሁ።

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድ ዴሞክራሲያዊና የበለፀገች አገር የመሆን ሰፊ እድል አሁንም አላት። ለምሳሌ በጣም በርካታ የደቡብ አፍሪካ ሕዝብ አሁን ድረስ ድሀ ነው፤ ነገር ግን፣ የደቡብ አፍሪካ ፖለቲካኞችና ሕግ አውጭዎች አገሪቱን ከአፖርታይድ ወደ እውነተኛ ዴሞክራሲ አሸጋግረዋታል፤ የደቡብ አፍሪካ ኢኮኖሚ እንዲያብብ ያደረገ ውጤት አስገኝቷል። ከገኘው ግንባርና ከተቃዋሚዎች ቆራጥ መሪዎች ካሉ፣ ኢትዮጵያ የደቡብ አፍሪካን መንገድ የማትከተልበት ምክንያት አይኖርም። ለእውነተኛ የመድብለ ፖርቲ ሥርዓት አቶ መለስና የሚመሩት ድርጅት መድረኩን ክፍት ካደረጉ፣ እና የእውነትና እርቅ

ኮሚሽን ከተቋቋመ፣ በተለያዩ ብሄሮች ምሁራን መካከል ያለው ታሪካዊ የጥላቻ ሽኩቻ/ፉክክር በእርግጠኝነት ይወገዳል፣ በመጨረሻም ድህው ስፍራውን ያገኛል።

ሀምሳ አራተኛ ዓመታቸው ላይ የሚገኙት አቶ መለስ ከጠ/ሚኒስትርነት ስልጣኔ ልለቅ እችላለሁ በማለት ለወራት የተደበላለቁ ምልክቶች ሲሰጡ ቆይተዋል። ሆኖም፣ የፖለቲካ ድርጅታቸው አባላት «እርሳቸውን በጣም በመውደዳቸው» ምክንያትና «ምትክ አልባ» አድርገው በመውሰዳቸው በሥልጣን እዲቆዩ «በጽኑ ጠይቀዋቸዋል» - እስከ 60ኛ የልደት-ቀናቸው ድረስ። ለቆራጥ መሪ ምን ያለ የልደት ስጦታ ነው! ሊያስብል ይችላል። ሆኖም፣ ከዚህ የፍቅር ጉዳይ በስተጀርባ፣ የተቀመረበት አደጋ አለ።

አቶ መለስ፣ ካለጥርጥር፣ የገዥው ግንባር ኢሕአዴግ - የአራት ክልላዊ ፓርቲዎች - የኦሮሞ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ኦሕዴድ)፣ ብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን)፣ የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ደኢሕዴን) እና የትግራይ ሕዝቦች ነፃ አውጭ ግንባር (ሕውሓት) - የፖለቲካ ቀማሪ ናቸው። ሆኖም ሕውሓት - የሶስቱ ፓርቲዎች መስራች እንደመሆኑ - ሁሉንም ነገር በብቸኝነት ተቆጣጥሮታል። የወቅቱን የኢሕአዴግ ውጣ ውረዶች መኖራቸው ሲጤኑ - ማለትም የኦባማ አስተዳደር፣ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ድርጅቶች፣ እየጨመረ ያለ ሕዝባዊ ቁጣ፣ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ዕድገት መውረድ እና ተቃዋሚ ፓርቲዎች - ለግንባሩ ቀጣይነት የአቶ መለስ መኖር ወሳኝ ነው። በመሆኑም፣ ግንባሩ ጠንካራ መሪው በሥልጣን እንዲቆይ መወሰኑ ትክክለኛ ውሳኔ ነበር። አቶ መለሰ የግንባሩን ውሳኔ ለጋዜጠኞች እንዲህ ብለው አብራርተዋል፡- «የፖሊሲ ቀጣይነት ለማረጋገጥና ለግንባሩ ግቦች ትግበራ ስኬት፣ ጥቂት ተጨማሪ ጊዜ አስፈላጊ መሆኑን ድርጅቱ ተሰምቶታል።»

ኢሕአዴግ በ2002 ለማሸነፍ ቆርጧል። ዋና ዋና ፓርቲዎች የገጠሟቸው አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲታዩ፣ በማሸነፉ ምንም ጥርጥር የለም።

**ምርጫ 2002**

ለኢሕአዴግ ፖለቲከኞች፣ የ2002 ምርጫ ከ1997 - በድህረ-ምርጫ በተፈጠረ ቀውስ መንግስትና ተቃዋሚ ኃይሎች እርስ በእርስ ከተናቆሩበት - ምርጫ የበለጠ ጠንካራ ይሆናል ተብሎ ተጠብቋል። በወቅቱ እንደተዘገበው፣ 200 የሚደርሱ ሰዎች ተገድለዋል፣ በርካታዎች ቆስለዋል። ተቃዋሚዎች፣ ደጋፊዎቻቸው፣ ጋዜጠኞችና የተወሰኑ የመያዶች መሪዎች ወደ እስር ቤት ተወርውረው «በአገር ክህደት» ተከሰው ነበር። ከምርጫው በኋላም አብዛኞቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሽባ ሆነው ነበር - በውስጥ እሰጥ አገባዎችና በመንግስት

ጣልቃ ገብነት፡፡ ብዙ የፖለቲካ እስረኞች፣ በኢትዮጵያ የመጀመሪያዋ ሴት የተቃዋሚ መሪ - ብርቱካን ሚዴቅሳ፣ አሁን ድረስ በአስቸጋሪ ዕስር ቤቶች ፍዳቸውን እየዩ ነው፡፡

# ክህደት ውርደት ይሁን!

**በአስቻለው በላይ**

እዚህ እኛ ሰፈር እድሜ የጠገቡ ወኔ የተሞሉ አንድ አረጋዊ አሉ፡፡ፀሀይ ሞቅ ስትል ዘወትር ከማይጠፉባት ልጅ አዋቂው ሴት ወንዱ ሰፈርተኛው በሙሉ የአብዬ መቀመጫ ከሚላት ድንጋይ ላይ ጭራቸውን እያወናጨፉ ይቀመጣሉ፡፡

አላፊ አግዳሚው እንደምን አደሩ እንደምን ዋሉ በማለት ሲጠይቃቸው «ዕድሜ ዘልዛላው ጆሮ አይሰማውን እየሰማ አይን የማያውን እያሳየ ይዞኛል አለሁ፣ይመስገነው ይሄው ከዛሬ ደርሻለሁ» በማለት ነው የሚመልሱት፡፡ ዘወትር ከጭራቸው እንቅስቃሴ ጋር አፋቸውም ይንቀሳቀሳል፡፡ ጠጋ ብሎ ለአዳመጣቸው እንጉርጉሮ ነው፡፡የበላይ ዘለቀን ሥም ደጋግመው ያነሳሉ፡፡ እንዲህ እንደ ዘወትር ፀሎት የበላይ ዘለቀን ሥም ማንሳታቸው ያለምክንያት አይሆንምና ልንጠይቃቸው ፈለግን አንድ ቀን ከእሳቸው ጋር ቆይታ አደረግን፡፡
አብዬ እንደምን አረፈዱ? ብለን እጅ ነስተን ሰላምታ ሰጥተን ቀረብናቸው፡፡ያው የተለመደውን «ዕድሜ ዘልዛሌ...» የሚለውን መልሳቸውን ሰምተን አጠገባቸው ተቀመጥን፡፡በቀጥታ ወደ ጥያቄያችን ከመግባት ዕድሜ ዘልዛሌ የሚለውን የዘወትር ቃላቸውን መነሻ ማድረግን መረጥንና «ዕድሜዎ ስንት ነው?» ስንል ጠየቅናቸው፡፡

«ይሄ ዘልዛላው ዕድሜ ነው ዘጠናውን ተሻግሯል» በማለት በአጭሩ መለሱልን፡፡እድሜ ዘልዛሌ የሚሉበትን ምክንያት እንዲነግሩን ጥያቄ አስከተልን፡፡ ሶስታችንንም ተራ በተራ ተመለከቱንና «አዬ ዕድሜ ዘልዛሌ ስንቱን አየንበት፤ ቁጥር ወደ ሰማይ ኑሮ ወደ መሬት» በሚል እንጉርጉሮ ጀመሩ፡፡ «እንኳን እና የትላልቆች የትናንትናዎቹ ሰዎች ፤የእናንተ የዛሬዎቹ እንቦቀቅላ ልጆች፤ የዕድሜ ሩጫ አይታችሁም ፡፡ ዕድሜ በየእለቱ ቁጥሩ ይጨምራል ኑሮ በየቀኑ መቀመቅ ይወርዳል፡፡እስቲ እኔን ተውትና እናንተ ነፍስ ካወቃችሁ በኋላ በየጊዜው የሚታየውን የኑሮ ውድነት አጢኑት ፡፡ግን እግዜር ደግ ነው፤ ሰው ባይባልም ወዝ አለው፤ ዕድሜ ለቻይና ኪሱ ባዶ ቢሆንም ለብሶና ተጫምቶ ሰው መስሎ ይውላል፡፡ማታ ሲመለስ ግን የቤቱን የሚያውቁት እሱና ፈጣሪ ብቻ ናቸው፡፡ቤት ገበና ከታች አይደል፡፡ ለነገሩማ እንዳንዱ ቤት የእኔን ዕድሜ ያስቆጠረና ቤት ሊባል የማይበቃ ነው፡፡ራዲዮና ተሌቭዥኑ ባንበላም መጥገባችንን ያወራሉ፡፡ ገበያ ተይዞ የሚወጣው ገንዘብ የመግዛት አቅሙ ከሞተ አመታት ቢቆጠሩም ኢኮኖሚው አድጓል ፤ሀገር በልፅጋል እያላችሁ ታወራላችሁ፡፡ ከውኃ ነው የሚገኘው የምትሉት መብራት ጠፍቶ ወደ እኛ ዘመን ተመልሳችሁ ከጨለማ ጋር መለማመድ ጀምራችሁ

ባለበት ሀገሪቱ ፈጣን እድገት እያስመዘገበች ነው ትላላችሁ::አያችሁ እድሜ ዘልዛላው ይህን ሁሉ ሀፍረት የጠፋበት ድርጊት ያሳያል:: ያሰማል::»...

ከመጣንበት ጉዳይ ውጪ ያልጠበቅነውን ሲነግሩን በተመስጦ ስናዳምጣቸው ቆየንና ዋናውን ጉዳያችንን አነሳን::ዘወትር የበላይ ዘለቀን ስም ሲያነሱ እንሰማለን ::«ዝምድና አላችሁ?ወይንስ በአርበኝነት ዘመን ተገናኝታችሁ ነበር?» አልናቸው ::

የበላይን ስም ሲሰሙ ሰውነታቸው ሲለዋወጥ ያስታውቅ ነበር::«አዬ እናንተ ልጆች ቁስሌን ባትነኩት ምንአለ?» አሉና «አርበኞች ተገድለው ባንዳው ተሸለመ፤ታሪክ ጎደፈ ሀገር ታመመ፤ንጉሱ ከባንዳ ፍቅር መስርተው፤ ስንቱን አርበኞች በሞት ቀጧቸው!»በማለት ከአንጎራጎሩ በኋላ እናንተ የዛሬ ልጆች ታሪክ የማታውቁና የማታውቁትንም የምትንቁ በመሆናችሁ እንጂ የበላይ ዘለቀ አገዳደል ትውልድ ሳይለይ ኢትዮጵያውያንን ሁሉ ሊያስቆጭ በተገባ ነበር:: አምስት አመት ሙሉ በዱር በገደሉ የተዋጋ፤ ጀግንነቱን የአገሩ ሰው ቀርቶ ፋሺስት ጣሊያን ሳይቀር የመሰከረለት፤ ለኢትዮጵያ ነፃነት መመለስ ታላቅ ተጋድሎ ያደረገ ጀግና፤ በሀገሩ መንግስት ሲገደል አያስቆጭም::አያስቆጣም ትላላችሁ በማለት እኛኑ መልሰው ጠየቁን::ያላሰብነው ድንገተኛ ጥያቄ ነበርና መልሳችን ዝምታ ሆነ::እሳቸውም ከእኛ መልስ ሳይጠብቁ ትረካቸውን ቀጠሉ::

ንጉሱ ከተፋፋመው ውጊያ መሐል ወደ ውጪ አገር መሄዳቸው ባልከፋ ነበር::ለነፃነታችን መገኘት ድጋፍ አስገኝቷልና::ተመልሰው መንግሥታቸውን ሲያፀኑ ግን አርበኛውን ገሸሽ አድርገው ከባንዳው ጋር መወዳጀታቸው ትልቅ ጥፋት ነበር:: በላይን ያስገደሉት ከንጉሱ የተወዳጁ ባንዳዎች ናቸው::

ከፈራጁ ጥፋት የአድራጊው ድፍረት፣

ገመድ አጠለቁ ከበላይ አንገት፤

ስለ ጀግንነቱ እንከን አይወጣለት፤

ፋሺስቱ እንኳን ሳይቀር የመሰከረለት፤

ባንዳ ተሰብስቦ ሞት አስፈረደበት፤

በላይ እንዴት ይሙት፤ ያ የሀገር ኩራት:: አሉና ሲቃ ተናነቃቸው::ስሜታቸው ወደ እኛም ተጋባና ለደቂቃዎች ፀጥ አልን:: አብዬ በመንግሥቱ ዘመንስ ቢሆን ሲሉ ነበር ሁላችንም ከነበርንበት ስሜት የነቃነው::መንግሥቱ ኃ/ማርም ስንቱን እበላ ባይ አጎብዳጅ በዙሪያው አሰልፎ አይደል ምትክ የለሽ ጀግኖችን የፈጀ:: ከጦር ሜዳ ዘልቀው ድል ያስጨበጡ ተዋግተው አዋግተው : ስንት ጀግኖች ናቸው የተረሸኑ ፀረ-አብዮተኛ እየተባሉ::አጎብዳጅ ሁሉ ወሬ አቀባባይ፤ ከተግባሩ የለ አለሁ አለሁ ባይ ከመንግሥቱ ሥር እየዳከረ፤ ስንት አስገደለ ስንት አሳሰረ:: መቼም ይሄ የቅርብ ጊዜ ድርጊት በመሆኑ የምታውቁት ይመስለኛል:: ከጄነራል አማን ጀምሩና ደርግ የበላቸውን የራሱን ሰዎች በአንድ በኩል፣በሌላ በኩል ደግሞ ከመንግሥቱ ጉያ ተሸጉጠው «ከጎድ መንግሥቱ ጋር ወደፊት! እያሉ ሲያላዝኑ ቆይተው

እሱን ለስደት ራሳቸውን ለሞት ለእስርና ለስደት የዳረጉትን ወኔ ቢሶች ሥም ደርድሩና አስተያዩት ። የቱ ሚዛን ይደፋል? በማለት ለጥያቄ የሄድነውን ሰዎች ቢጠይቁንም በዛችው ቅፅበት መልስ አልፈለጉምና ንግግራቸውን ቀጠሉ።

የኢህአዴግ ሰዎችም ቢሆኑ ከጫካ ጀምረው ብዙ አሳልፈው እንደመጡ ነው የሚነገረው። ያኔ! በስንት ዓመተ ምህረት ነበር? መከፋፈል ፈጥረው «በስብሰናል ምንትስ» እያሉ ለጆሮ የሚቀፍ ቃላት ይናገሩ በነበረበት ወቅት አብረው ተሰልፈው፤አለን አለን ብለው፤ ጓደኞቻቸውን ያስበሉ ድንገት ተቀልብሰው፤ እንዳለፈው ጊዜ ባይገዳደሉም እንናተም ታውቃላችሁ የተፈጸመውን የታሰሩትንም ሆነ ለሹመት የበቁትን።»አሉንና «እናንተ ጉደኛ ልጆች እየነከከችሁ ብዙ አሰስወራችሁኝ። ጆሮ ልትጠቡ ይሆን እንዴ ዛሬ አለወትሮአችሁ እንዲህ በቁም ነገር የመጣችሁ?» አሉና ከእኛ መልስ ሳይጠብቁ «ብትሆኑስ ምን ታመጣላችሁ መንግስት ለመገልበጥ ያስባል አትሉኝ። መንግሥታችን ደግሞ በሥልጣኑ- መንግሥቱ ለመጣበት እንጂ ቀልድ የማያውቀው፤ ለሌላ ለሌላው ሆደ ሰፊ ነው» አሉና «ልቀልድ ብዬ እንጂ የማውቃችሁ እዚሁ ያሳደግኋችሁ ልጆች አይደላችሁ?» አሉንና ወጋቸውን ቀጠሉ።

«የበላይን ያህል የሚያንገበግበኝ...» አሉና በተመስጦ ሁላችንንም ቃኘት ከአደረጉና ለማዳመጥ ያለንን ጉጉት ከተመለከቱ በኋላ የዶ/ር አሥራት ነገር ነው አሉ አታውቋቸውም እንዴ አሉን። እርስ በርስ ተያየንና «ፐ/ር አሥራትን ነው? እሳቸውን ከሆነ ብዙም ባይሆን እናውቃቸዋለን» አልናቸው።

«አዎ ፐ/ር አስራት ታዋቂው ሐኪም። የንጉሰ ነገሥቱ ሐኪም ስለነበሩ ክቡር ዘበኛ ሐኪም ቤት ይመጡ ነበር። እኔም ያየኋቸው እዛ ነው። ክቡር ዘበኛ እንደነበርኩ ታውቁ የለ?»አሉ። «አዎ»አልናቸው ሶስታችንም በአንድ ላይ። በሰፈር ሲወራ ሰምተናልና።ማወቃችን ሳያስደስታቸው አልቀረም።

«የኮሩ ኢትዮጵያዊ የተደነቁ ባለሙያ ሀኪም ነበሩ። ታዲያ በዚህ በእናንተ ዘመን በመጣው ለውጥ አማራው ተጠቃ አሉና «የመላው ዐማራ ሕዝብ ድርጅት »የሚባል ፓርቲ መስርተው ሀኪሙ ፖለቲከኛ ሆኑ።

ከጎናቸው የቆመ ሁሉ እውነተኛ ታጋይ መስሏቸው።የሚያወራው ሁሉ ደፍሮ የሚሰራ መስሏቸው፡ የሚፎክረው ሁሉ ጀግና ያለመሆኑን ሳይረዱ ቀርተው ከብዙዎች ጋር ተሰልፈው ግን ብቻቸውን ተገኝተው ተጠቁ። ታስረው ተንገላቱ። የስንቱን ህይወት የታደጉት ሐኪም ለእሳቸው የሚሆን ሐኪም አጥተው ሞቱ። እሳቸው ወደ እስር ቤት ሲገቡ ስንቱ በረገገ። ስንቱ ከዳ። ስንቱ አገር ጥሎ ኮበለለ።አዬ ሀበሻ። ይህንንስ ታሪክ አታውቁም?» አሉና ጠየቁን ።ግን መልስ አልጠበቁም። በተመስጦ እያዳመጥናቸው መሆኑን ሲገነዘቡ ቀጠሉ።

«ይሄውላችሁ የሰፈራችን ልጅ ብርቱካን ላይም የተፈጸመው ተመሳሳይ ድርጊት ነው። የእኛ ሰፈር ፈረንሳይ ያበቀላት የሴት ወንድ ጀግና! ወይኔ አደፍርስ እናቷ ልጅ ወልጃለሁ ይበሉ። ስም አነሳት» አሉና በስጨትጨት አደረጋቸው። እኛም ተደናግጠን ዝም አልን።

«የትግል አጋሮቼ ያለቻቸው ሴት ናት ብለው ንቀው አትመራንም አሏት::የመሪነት ብቃቷን ሲያዩ ቆራጥነቷን ሲረዱ ደግሞ ገና ለገና በፖሊስ ተጠራች ብለው «የራስሽ ጉዳይ» እንዳሏት ሰማን:: ይህ ክህደት አይደለም::ደግፈዋት መቆም ቢሳናቸው ወይንም ቢያስፈራቸው ዝምታ ማንን ገደለ::ቦቅቧቃ ሁላ:: እነዚህ ናቸው አሁን አገር እንመራለን ሕዝብ እናስተዳድራለን ምረጡን የሚሉት? በላይን ያበቀለች አገር እነዚህን ታፍራ?ይህች አገር ወኔ ተላብሶ በፅናት ቆሞ ለሚያገለግላት ሳይሆን ከሞቀው ተጠግቶ ከመጣ ከሄደው ተመሳስሎ ለሚያድረው ነው የምትሆነው::«እማማ ኢትዮጵያ ሞኝ ነሽ ተላላ፤ የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ» ተብሉ ሲዘፈን ሰምታችኋል አይደል?» አሉን::ሁላችንም በአዎንታ ራሳችንን ነቀነቅን:: በበላይ ዘለቀ መገደል የተዘፈነ ቢሆንም በየጊዜው ለሚፈፀሙ ተመሳሳይ ድርጊቶች የሚሰራ ነው::

ብርቱካን ዳኛ ሆና የሰራችውን ታውቃላችሁ::ተመሳስዬ ልኑር ብትል ዛሬ የት በደረሰች ነበር:: በጥብቅና ሥራ ብትቀጥልም የተንደላቀቀ ኑሮ መኖር ትችል ነበር:: ከእስር ቤት ከወጣች በኋላ በሄደችበት አገር ብትቀርም ተንቀባራ በኖረች ነበር:: የመንግስት ማስፈራሪያ አስፈርቷት የተባለችውን ብትፈፅምላቸው ኖሮም ላትታሰር ትችል ነበር::

እሷ ግን ቃሏን አክብራ እምነቷን ጠብቃ ከሄደችበት ተመለሰች:: በአላማዋ እንደፀናችም እስራትን ተጋፈጠች::በትግል አጋሮቿ ግን ተከዳች::ግና ምን ያደርጋል የበላይ እርግማን ዛሬ ድረስ ዘልቋል:: አርበኛው ተገድሎ ባንዳው ከተሾመ፤ ሀቀኛው ተገፍቶ ከሀዲው ከታደመ፣እውነት ቦታ አጥታ ከነገሰች ሀሰት፤ ይህች ሀገራችን ከእንግዲህ ምን ቀራት:: በላይም ሲረግማት ልጅ አይውጣልሽ ነው ያላት:: እናስ ምን ትላላችሁ በበላይ ላይ የተፈጸመውን ክህደት የሚያስታውሱ ድርጊቶች እለት በእለት እየተፈጸሙ ነው በላይ ከልቤ ሊወጣ ያልቻለውና እለት በእለት የማነሳው::«ኢትዮጵያ አገሬ ሞኝ ነሽ ተላላ፣ የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ» የሚለው ይኸው በዘፈንም በተግባርም ከእናንተ ደርሷል:: ከእናንተ ለሚቀጥለው ትውልድ እንዳይሸጋገር ግን እግዜሩ ይርዳን» አሉ:: ከጠበቅነው በላይ ሰምተን ካሰብነው የላቀ ቁም ነገር አግኝተን አመስግነን ተለየናቸው::በዚህ ትውልድ ክህደት ውርደት ይሁን የእኛ መልእክት ነው::

# የካርቦን ቅነሳ ብቻውን ግቡን አይመታም

*በብጅሮን ሎምቦርግ*

በዚህኛው ዓመት ታህሳስ ወር ውስጥ የዓለም መሪዎች በኮፐንሀገን የአየር ንብረት ለውጥን አስመልክተው በሚያካሂዷቸው ጉባኤዎች፣ ዓለምን ለክፍለ ዘመናት የሚነኳት ውሳኔዎችን ያስተላልፋሉ:: ከጉባኤዎቹ ሶስት ወራት አስቀድሞ እነዚህ ውሳኔዎች ምን መሆን እንዳለባቸው የሚዳስሱ ጠንካራ ውይይቶች አለመኖር በአስደንጋጭ መልኩ

ይስተዋላል፡፡ ለክርክር በአብዛኛው የሚያልፌው ምንድን ነው ከባቢ አየር ለውጥ ተጨባጭ አይደለም ብለው በሚያምኑና ምድርን ያጠፉታል ብለው በተቀበሉ መካከል የሚደረግ የጫጫታ ግጥሚያ ነው፡፡ ይህ እንግዲህ ምንድነው የሚመስለው ከተባለ በአጠቃላይ ሁላችንም ወይ «ከሃዲዎች» አልያም «አማኞች» እንደሆንን ነው፡፡

የአየር ንብረት ለውጥ ተጠቃሽ ሳይንቲስቶች ጠንቃቃ ስራ የሚያሳየው የሰው እንቅስቃሴ ምድርን እያሞቃት መሆኑን ነው፡፡ ያንን ነጥብ ከአስር ዓመታት በላይ አንስቼዋለሁ፡፡ ሆኖም ጥናቱ በተጨማሪ የሚጠቁመው አብዛኛዎቹ በፊልሞችና በሚዲያ የሚቀረፁ እጅግ አስደንጋጭ ሁነቶች - ለምሳሌ ስድስት ሜትር ከፍታ የውሃ ግድግዳ - ጭራሽ የመከሰት አጋጣሚ እንደሌላቸው ነው፡፡ በይበልጥ፣ በብቸኝነት የቀረበ ፖሊሲ የሚመስለው የበለፀጉ አገራት የካርቦን ልቀት እንዲቀንሱ ጥሪ የሚያቀርበው ነው (ግዙፍ ከተቀረው በይሻሻላል)፡፡ ሌሎች በይበልጥ ተስፋ ያላቸው ሀሳቦች ከነጭራሹ በማይጤኑበት ሰዓት፣ አካሄዱ መምከኑ አይቀሬ ነው፡፡

ከዚህ ቀደም ልቀት መቀነስ ሳይሳካ ቀርቷል፡፡ በ1997 (እ.ኤ.አ) በኪዩቶ የዓለም መሪዎች የ«ግሪን ሀውስ ጋዝ» ልቀትን በ5.2 በመቶ ከ1990 በታች በ2010 ለመቀነስ ቃል ገብተው ነበር፤ ሆኖም ያን ግባቸውን 25 በመቶ ያህል ድረስ አያሳኩም፡፡ ለኮፐንሀገኑ ጉባዔ የተወሰኑ የፖሊሲ አውጭዎች አሁን ባለው የልቀት መቀነስ ላይ እስከ 2050 ድረስ በ80 በመቶ ቅነሳ ይደረግ ሲሉ ጥሪያቸውን እያቀረቡ ነው፡፡ ይህ ግብ በይበልጥ የመሳካት እድል አለው ብሎ ለማሰብ የሚያስችል ጥቂት ምክንያት ነው ያለው፡፡ የአሜሪካ «ኬፕ-ኤንድ- ትሬድ» ሕግ በሴኔቱ ከፀደቀ ለአየር ንብረት ለውጥ የሚኖረው አስተዋጽኦ እምብዛም ነው፡፡ መላው የበለፀገው ዓለም ተመሳሳይ አዋጅ ነገ ቢያፀድቅ እንኳን የሙቀት መጠኑ እኤአ በ2100 ዝቅ የሚለው በ0.22 ዲግሪ ሴልሺየስ ብቻ ነው፡፡

በተመሳሳይ፣ በኢንዱስትሪ የበለፀጉ አገሮች በጠቅላላ እጅግ አስደንጋጭ ልቀቶችን የመቀነስ ግባቸውን ቢያሳኩ እንኳን፣ ስኬቱ እውን የሚሆነው በብልጽግና ላይ ግዙፍ መስዋዕትነት በመክፈል ነው፡፡ አየርላንድ በሚገኘው የምርምር ተቋም («Economic and Social Research Institute») ተመራማሪ የሆነው ሪቻርድ ቶል እንደሚለው፣ በአውሮፓ ሕብረትና በቡድን 8 ቃል እንደተገባው የዓለም ሙቀትን በ2 ዲግሪ ሴሊሺየስ ለመቀነስ የካርቦን ልቀትን አማራጭ አድርጎ መውሰድ በክ/ዘመኑ መጨረሻ 12.9 በመቶ «ጂዲፒ» የሚያስወጣ ነው፡፡ ያ በዓመት 40 ትሪሊዬን የአሜሪካ ዶላር ወይም በክ/ዘመኑ መጨረሻ ለእያንዳንዱ ሰብዓዊ ፍጡር ከ4000 የአሜሪካ ዶላር በለይ ይደርሰዋል ማለት ነው፡፡ እንዲያም ሆኖ መሰል እርምጃዎች በከፍተኛ ሙቀት ምክንያት የሚደርሰውን ጉዳት ለማዳን የሚቻላቸው 1.1 ትሪሊዬን የአሜሪካ ዶላር ብቻ ነው፡፡ ፈውሱ ከህመሙ የበለጠ የሚያም ነው የሚሆነው፡፡

ለዓለም ሙቀት የተለያዩ ምላሾች ለመስጠት ጥቅሞችና ወጭዎች እንዲጠኑ በ«ኮፐንሀግን ኮንሰንሰስ ማዕከል» ኮሚሽን ከተደረጉ ተከታታይ የጥናት ወረቀቶች አንዱ የሆነውን ያቀረበው የቶል ጥናት፣ በስፋት ከተወራለት ከኢኮኖሚስቱ ኒኮላስ ስተርን ሪፖርት ጋር የሚቃረን ሊመስል ይችላል:: ያ ሪፖርት ከቶል ጥናት በተለየ የካርቦን ልቀት ወጭን በተመለከተ ዝቅተኛ ግምት ተጠቅሟል፤ የዓለም ሙቀትን የሚመለከት የካሳ መጠንን በተመለከተ ደግሞ ከፍተኛ ግምቶችን ተጠቅሟል:: ቢሆንም ስተርን በቅረቡ ትክክለኛው ውጭ እርሱ በመጀመሪያ ካገኘው ውጤት ሁለት እጥፍ ሊሆን መቻሉን ተቀብሏል:: ይህም ከቶል ሪፖርት ጋር ተስተካካይ የሚሆን ነው:: አብዛኞቹ ኢኮኖሚስቶች ከሚያስቀምጡት በበለጠ፣ የስተርን ሪፖርት በተጨማሪ የሚገምተው ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች ከልቀት መቀነስ እንደሚገኙ ነው::

በአዎንታዊ ጐን ሁለት አማራጮች ጐልተው ይታያሉ:: አንዱ አማራጭ በአየር ንብረት ኢንጂነሪንግ ላይ መለስተኛ መዋዕለ-ንዋይ ፈሰስ ማድረግ ነው፤ የሙቀት መጨመርን የሚያዘገዩና በዚህም የሙቀት መጠንን ለመቀነስ የሚያስችሉ ሰው ሰራሽ መንገዶችን መከተል:: ለምሳሌ፣ አቶማቲክ ጀልባዎች ደመናዎችን ብርሃናማ ለማድረግና በዚህም የበለጠ አንፀባራቂ እንዲሆኑ፣ ተፈጥሮአዊ ሂደትን ለማፋጠን፣ የባህር ውሃ ወደ አየር እንዲረጩ ማድረግ ይቻላል::

ምድርን የሚመታትን የፀሀይ ብርሃን 1 ወይም 2 በመቶ ያህሉን መልሶ ወደ ከባቢ ማንጠር በቅድመ-ኢንዱስትሪ ዘመን ይለቀቅ ከነበረው «ግሪን ሀውስ ጋዝ» ሁለት እጥፍ እስከሚደርስ ሙቀት ሊያስወግድ የሚችል ነው:: 9 ቢሊዮን ዶላር የሚደርስ ወጭ ለቴክኖሎጂው ምርምርና ልማት ማዋል በከባቢ ሙቀት ከሚደርሰው ጉዳት 20 ትሪሊዮን ዶላር ሊያድን የሚችል ነው:: በምሳሌ ለማስቀመጥ ያህል፣ የአሜሪካ ዓመታዊ የአየር ንብረት ምርምር ባጀት 6 ቢሊዮን ዶላር ነው፤ ለአስራ ስምንት ወራት ብቻ በዚህ ተስተካካይ ወጭ በሚቀጥለው ክ/ዘመን ሌላ ተጨማሪ የሙቀት መጨመርን ልናስወግድ እንችላለን:: የአየር ንብረት ኢንጂነሪንግ ስነ-ምግባራዊና ሎጂስቲካዊ ጉዳዩችን ከፍ ሊያደርግ ይችላል፣ ለውይይት ዋሰትና ነው፤ ሆኖም፣ ለዓለም ሙቀት ምላሽ ርካሽና ውጤታማ አማራጭንም መቀበል አለብን::

«አረንጓዴ» የኃይል ሀብቶችን በተመለከተ ለጥናትና ለልማት የመዋዕለ-ንዋይ ፈሰስ ማድረግ እንዲቻል ዓለም አቀፍ ስምምነት ማድረግ ሁለተኛው አማራጭ ነው:: የነዳጅ ኃይል ጥገኝነትን ለመቀነስ በጣም ከካርቦን ነፃ ኃይል ያስፈልገናል - በአየር፣ በፀሃይ ኃይል የሚያመነጩና ሌሎች ቴክኖሎጂዎች በአሁኑ ወቅት ካሉበት ደረጃ በብዙ መቶዎች እጥፍ መጨመር:: በ«አረንጓዴ» ኃይል በየዓመቱ 100 ቢሊዮን ለምርምር ፈሰስ ማድረግ የከባቢ ለውጥን በአንድ ክ/ዘመን ወይም አካባቢ ትርጉም ባለው መልኩ ልንጠግን እንችላለን ማለት

ሊሆን ይችላል፤ ይህ ማለት ደግሞ የሚደረገው የመዋዕለ-ንዋይ ፈሰስ እያንዳንዱ ዶላር በአየር ንብረት ለውጥ ይጠፋ የነበረን 11 ዶላር ወጪ ያተርፍልናል፡፡

ከዚያ ይልቅ ወደ ካርቦን ልቀት ቅነሳ ዘመቻ ከገባን፣ ከፍተኛ ከባቢያዊ ጉዳት በራሳችን ላይ እናደርሳለን፤ ጎጂ ሙቀትን ሳናስወግድ፡፡ የአየር ንብረት ለውጥን ለመመከት በሚቻለን መጠን ማለም አለብን፡፡

***(ብጆርን ሎምቦርግ ዴንማርክ በሚገኘው «Copenhagen Consensus Center» ዳይሬክተር ነው፡፡)***

# ሞቲቬሽን

## <u>ተስፋ</u>

**በባንቿወሰን ወልደየሱስ**

ሁሌም ቢሆን ተስፋ አለ፡፡ ይሄ ተስፋ የምንለው ነገር ትልቅም ይሁን ትንሽ መልካም ነገር ነው፡፡ ተስፋ ባይኖር ህይወት መክበድ ብቻ ሳይሆን ምናልባት ደስ የሚል ትርጉምም ላይኖረው ይችል ነበር፡፡ የማየት ወይም ያለማየት ጉዳይ ነው እንጂ በሁሉም ቦታ ላይ እና በማንኛውም ጊዜ ተስፋ አለ፡፡ በሆነ ቦታ እና ጊዜ ላይ ሆነን ተስፋን ማየት ካልቻልን ግን የዛን ያለንበትን ቦታ ሁኔታ የበለጠ ለማሳመር ወይም ወደፊት ለመሄድ አስቸጋሪ ነው፡፡ ምክንያቱም ተስፋ ወዴት እንደምንሄድ የሚነግረን አቅጣጫ ነውና ያለሱ ወዴት መሄድ እንችላለን? ጭላንጭልም ይሁን ወይም በመጠኑ ተለቅ ያለ ማንኛውም ወደፊት የሚያንቀሳቅስ ነገር ተስፋ የሚሰጥ ነገር ነው፡፡

ተስፋ ከማይሰጡ ብዙ ነገሮች ላይ ከማተኮር ይልቅ ተስፋ የሚሰጡ ነገሮች ላይ ማተኮር ለብዙ ነገር ይጠቅማል፡፡ አንደኛ ተስፋን ማየት ካልቻልን ወይም ካልፈለግን እኛው ራሳችን ተስፋ እንቆርጣለን፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ደግሞ ያለንን ኃይል መጠቀም አንችልም፡፡ ይሄ ብቻ ሳይሆን ብዙ ተስፋ ስለማናደርግ ፍላጐትም አይኖረንም፡፡ ፍላጐት ደግሞ ወሳኝ የሆነ ለሁሉ ነገሮች ማማር እና መሰራት መሰረት ነው፡፡ ሌላው ተስፋ የሚሰጡ ማንኛውም ነገሮች ላይ ማተኮር የሚጠቅመው የአቅማችንን ያህልና ከዛ በላይ የምንሰራው በዚህ ሁኔታ ውስጥ ስንሆን ነው፡፡ ይህ ሁኔታ አቅጣጫ ያስያዘናልና አውቀነውም ይሁን ሳናውቅ ከፍተኛ እገዛ ያደርግልናል፡፡

አዎ በሁሉም ሁኔታ ውስጥ ተስፋ አለ፡፡ ለምሳሌ አንድ ሺህ ተስፋ የሚሰጡ ነገሮች ቢኖሩ እና ምናልባት አንድ ተስፋ የሚሰጥ ነገር ቢኖር ወይም የዛ አንድ ተስፋ ግማሽ አካሉ ተስፋ ከሰጠን እዛ ላይ ማተኮር ብልህነት ነው፡፡ ነገ ከዛሬ የተሻለ እንሰራለን ብለን ተስፋ እናደርጋለን፣ ይሄን እናገኛለን ይሄን ደግሞ እንሰጣለን ብለን ተስፋ እናደርጋለን፣ የመሳሰሉት፡፡ ተስፋን በሁሉ ነገር ውስጥ የሚፈልግ እና ያን ተስፋ በተግባር እውን ለማድረግ የሚሞክር እና ተስፋን የሚያፈልግ ሰው በሁኔታቸው፣ በድርጊታቸው እና በሕይወታቸው እንደ ቀን እና ሌሊት የተለያዩ ናቸው፡፡ አንዱ ዛሬ ከሰራው በተጨማሪ መጨመር እና ማሻሻል የሚችለው ነገር ስለሚታየው ያንን ተስፋ እውን ለማድረግ ነገ ላይ ይጥራል፡፡ ሌላው ዛሬ ከሰራው በተጨማሪ ሌላ ሊጨምር የሚችለው ነገር ስለማይታየው የዛሬ ስራው በቂ ነው ብሎ ያስባል፡፡ አንዱ ለቤተሰቡ ዛሬ ደስ የሚል ፍቅር ቢሰጥም ነገ ላይ ከዛ የበለጠ ፍቅር እሰጣለሁ ብሎ ያስባል፡፡ ሌላው በቂ ፍቅር ዛሬ ላይ እየሰጠሁ ስለሆነ ነገ ተጨማሪ ፍቅር ያስፈልግ ይሆናል ብሎ አያስብም፡፡ አንዱ ዛሬ ያገኘሁት ነገር ስለማይበቃ ነገ የበለጠ ለማግኘት እሰራለሁ ይላል፡፡ ሌላው ነገ ላይ የበለጠ እና የተሻለ ነገር አገኛለሁ ብሎ ተስፋ ስለማያደርግ ተጨማሪ ነገር አያደርግም፡፡ በዚህም ምክንያት ነገ ላይ ብዙ መስጠት አይኖርም፡፡ ይሄ ባህሪይ እና ድርጊት ሙሉ በሙሉ የሌላኛው ተስፋ የሚያደርገውን ሰው ተቃራኒ ነው፡፡ ምክንያቱም ተስፋ የሚያደርግ ሰው ሁሌም ቢሆን ብዙ ይሰጣልና፡፡

ዛሬ ከምናያቸው ማንኛውም ነገሮች ላይ ነገን የተሻለ ነገር መጠበቅ ዛሬ የሰራነው ነገር ጥሩ አይደለም ማለት ሳይሆን ሁላችንም ብንሆን ለተስፋ እድል እየሰጠን ነው፡፡ መቼም ቢሆን የሚሰራ ስራ አያልቅም፣ መቼም ቢሆን ፍቅር አይበዛም፣ የተሻሉ ነገሮች ተስፋ ማድረግ አይረፍድም፡፡ ተስፋ ካለ የበለጠ ስራ መስራትን፣ ብዙ ፍቅር መስጠትን፣ ብዙ ማለምን፣ የበለጠ ማደግን እና የመሳሰሉት ነገሮች ይኖራሉ፡፡ የማንኛውም መልካም ነገሮች መብዛት ማንም አይጠላም፡፡ እንደውም እጅግ በጣም ተፈላጊ ነገሮች ናቸው፡፡ ግን የያዝናቸው ወይም ልናገኛቸው የምንፈልጋቸው ማንኛውም መልካም ነገሮች እንድንያዛቸው እና ከያዝናቸውም በኋላ እንድናሳድጋቸው ተስፋን ከታላቻው እንደ ትልቅ ድጋፍ ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ ጥሩ ላልሆኑ ነገሮች ብቻ ሳይሆን ጥሩ ይሆናሉ ብለን ተስፋ የምናደርገው እና ተስፋ ይዘን የምንሰራው ጥሩ ለሆኑም ነገሮች የበለጠ ጥሩ እንዲሆኑ ተስፋ ያስፈልጋል፡፡ ጥሩ የሆነ ነገር መቼም ቢሆን ማብቂያ የለውምና፡፡

ተስፋ ከፍቅር፣ ከእምነት፣ ከስራ፣ ከእድገት እና ከሌሎች ከብዙ ነገሮች ጋር አብሮ ይሄዳል፡፡ ሊታወቀን ወይም ላይታወቀን ይችላል ግን ነገን በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ስናስብ ተስፋ ከጀርባችን አለ፡፡ ይሄ ተስፋ ትንሽም ይሁን ትልቅ ያው ተስፋ ነው፡፡ ተስፋ የምናደርገው ነገር አናሳ መሆን ሳይሆን ዋናው ቁም ነገር ተስፋን መያዛችን ነው፡፡